የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

፴፩ኛ ዓመት ቁጥር ፶፱
አዲስ አበባ ነሀሴ ፰ ቀን ፪ሺ፲፯

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No. 59
ADDIS ABABA, 14th August, 2025


**ማውጫ**


አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፹፱/፪ሺ፲፯

የኢትዮጵያ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት አዋጅ ………….....................ገጽ ፲፱ሺ፲፮


**Content**


Proclamation Number 1389/2025

Ethiopia's Overseas Employment Proclamation…......................... Page 19016


## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፹፱/፪ሺ፲፯
## የኢትዮጵያ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት አዋጅ

በሀገር ውስጥ ምቹ የሥራ ዕድሎች የሚስፋፋበትን ሁኔታ ለመፍጠር መንግሥት የሚያደርገው ጥረት እንደተጠበቀ ሆኖ ወደ ውጭ ሀገር በመሄድ ለመሥራት ፍላጎት ያላቸው እና ብቁ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን መብታቸው፣ ደህንነታቸው እና ክብራቸው ተጠብቆ ባላቸው ችሎታና አቅም ሠርተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል አስፈላጊ በመሆኑ፤

የሥራ ገበያ ፍላጎትን መሰረት ባደረገ መልኩ ከተቀባይ ሀገሮች እና ሕጋዊ ድርጅቶች ጋር የሁለትዮሽ ስምምነት፣ የመግባቢያ ሰነድ ወይም አግባብነት ያለው ስምምነት በመፈራረም ሕጋዊ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪትን በማጠናከር በሰው የመነገድና ሰውን በሕገ ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ጠቃሚ መሆኑ በመታመኑ፤

## Proclamation Number 1389/2025
## Ethiopia's Overseas Employment Proclamation

**WHEREAS**, notwithstanding the Government's commitment to creating a favorable domestic condition for promoting employment opportunities, it has been deemed imperative to protect the rights, safety and dignity of Ethiopians seeking overseas employment, commensurate with their qualifications and abilities, and to facilitate their rightful benefit therefrom;

**WHEREAS**, it is believed that concluding labor-market-driven bilateral agreements, memorandum of understanding and other relevant agreements with receiving countries and legal organizations strengthens legal pathways for overseas employment and serves as a vital instrument in the prevention and suppression of trafficking in persons and the smuggling of persons;




https://ethiodata.et/

የግሉ ዘርፍን ጨምሮ ሌሎች አግባብነት ያላቸው አካላት በውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት አገልግሎት አሰጣጥ ሊኖራቸው የሚገባውን ተሳትፎ በሕግ መወሰን በማስፈለጉ እና ለዚህም መንግሥት የሚኖረውን ክትትልና ቁጥጥር ማጠናከር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት አገልግሎት ለዜጎች ቀልጣፋና ተደራሽ መሆን እንዲችልና ሕገወጥ የሥራ ስምሪትን መቀነስ የሚያስችል በቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ሥርዓት ተግባራዊ በመደረጉና ይህንን በሕግ መደንገግ በማስፈለጉ፤

የሰለጠነ በከፊል የሰለጠነ እና የትምህርት ዝግጅት የሌላቸውና በልምድ የተገኘ ክህሎት ያላቸውን ሠራተኞች ለማሰማራት የሚያስችል ግልጽ የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት የዜጎችን መብት፣ ክብርና ጥቅም የሚያስከብር ብሎም በውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ሀገራዊ ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሕግ መደንገግ በማስፈለጉ፤

የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪትን በተመለከተ ኢትዮጲያ ከተቀበለቻቸው የዓለም አቀፍ ስምምነቶች ጋር የተናበበ እንዲሆን በማስፈለጉ፤

በስራ ላይ ያሉት የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ሕጎች የዘርፉን ዓላማዎች በተሟላ መልኩ ለማሳካት የማያስችል በመሆኑ እና በአዲስ የሕግ ማእቀፍ መተካት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

**WHEREAS**, it has become essential to define the role of the private sector and other pertinent entities involved in overseas employment services, and to enhance the Government's follow-up and monitoring of overseas employment services;

**WHEREAS**, for the purpose of ensuring efficient and accessible overseas employment services for citizens and mitigating unlawful overseas employment, a technology-oriented system has been established; and it is now imperative to codify it into law;

**WHEREAS**, it has become necessary to enact legal regime that facilitates the overseas employment of skilled, semi-skilled and experienced-based qualification through a transparent system, thereby protecting their rights, dignity and interest, while enhancing the country's competitiveness in overseas employment;

**WHEREAS**, it has become essential to establish a legal framework governing overseas employment that complies with international treaties Ethiopia has ratified;

**WHEREAS**, because the pre-existing overseas employment laws could not fully realize the objectives of the sector, it has become necessary to replace them with a new legal framework;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

https://ethiodata.et/

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፹፱/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "**ሚኒስቴር**" ማለት የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ነው፤

፪/ "**ኤጀንሲ**" ማለት ከሚንስቴሩ በተሰጠው ፈቃድ መሰረት ሠራተኛን በሕጋዊ መንገድ በውጭ ሀገር ለሥራ ሥምሪት ለአሠሪ የማቅረብ አገልግሎት የሚሰጥ መንግሥታዊ ያልሆነ አካል ነው፤

፫/ "**ፈቃድ**" ማለት በግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝነት ሥራ ላይ ለመሰማራት ብቁ ለሆኑ ኤንሲዎች በሚኒስቴሩ የሚሰጥ ሠራተኛና የውጭ ሀገር ሥራ የማገናኘት ሥራ ፈቃድ ምስክር ወረቀት ወይም የብቃት ማረጋገጫ ነው፤

፬/ "**አሠሪ**" ማለት አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎችን በዚህ አዋጅ በተመለከተው የሥራ ውል መሠረት በኤጀንሲ አማካኝነት፤ መንግሥት-ለመንግሥት በሚደረግ ስምምነት ወይም በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት በቀጥታ ቅጥር የሚያሰራ ሰው ነው፤

## PART ONE

## GENERAL

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as "Ethiopia's Overseas Employment Proclamation No 1389/2025".

**2. Definition**

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1/ "**Ministry**" means the Ministry of Labor and Skills;

2/ "**Agency**" means a non-governmental entity licensed by the ministry to legally provide a worker to employer for overseas employment;

3/ "**License**" means a certificate of deployment license or of competence issued by the Ministry to eligible Agencies, allowing them to engage in providing overseas employment;

4/ "**Employer**" means any person who employs one or more persons through an Agency or through Government to Government arrangement, or through direct employment, in accordance with this Proclamation;

https://ethiodata.et/

፭/ "**ሠራተኛ**" ማለት በዚህ አዋጅ በተመለከተው የሥራ ውል መሠረት ከአሠሪ ጋር በቅጥር ላይ የተመሠረተ የሥራ ግንኙነት ያለው የሰለጠነ ወይም በከፊል የሰለጠነ ግለሰብ ሲሆን፣ እንደየአግባቡ በውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት የቅጥር ሂደት ላይ ያለ ሰውን ይጨምራል፤

፮/ "**ቀጥታ ቅጥር**" ማለት የመንግሥታዊ አካል ወይም የኤጀንሲ አገልግሎት ሳይሰጥ አሠሪውና ሠራተኛ በራሳቸው በሚያደርጉት ግንኙነት የሚፈፀም ቅጥር ነው፤

፯/ "**የሥራ ሁኔታ**" ማለት በአሠሪና ሠራተኞች መካከል ያለ ጠቅላላ ግንኙነት ሲሆን ይህም የሥራ ሰዓትን፣ ደመወዝን፣ ፍቃደኝነትን፣ ሠራተኞች ከሥራ በሚሰናበቱበት ጊዜ የሚገባቸውን ክፍያዎች፣ ጤንነት፣ ደህንነት፣ በሥራ ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው ሠራተኞች የሚከፈል ካሳ፣ እንዲሁም ሌሎች በሥራ ላይ የሚያጋጥሙን የሥራ ሁኔታዎች ያጠቃልላል፤

፰/ "**የሥራ ላይ አደጋ**" ማለት ሠራተኛ ሥራውን በማከናወን ላይ ሳለ ወይም ከሥራ ጋር ግንኙነት ባለው ሁኔታ ከራሱ ውጭ በሆነ ምክንያት ወይም ሥራውን ለማከናወን ባደረገው ጥረት ምክንያት በአካሉ ወይም በአካሉ ማንኛውም ክፍል ተፈጥሮአዊ እንቅስቃሴ ላይ በድንገት የደረሰበት ጉዳት ነው፤

፱/ "**የሙያ ብቃት ማረጋገጫ**" ማለት አንድ ሠራተኛ ለሚቀጠርበት ሥራ የመሥራት ብቃት ያለው ስለመሆኑ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ተመዝኖ የሚሰጥ ማስረጃ ነው፤

5/ "**Worker**" means an individual engaged in contractual relationship with an employer or Agency, possessing either skilled, semi-skilled or experience-based qualifications, in accordance with this Proclamation, and it may, as the case may be, include a person who is undergoing an overseas employment process;

6/ "**Direct Employment**" means an employment relationship between an employer and a worker without the involvement of a government organ or an Agency;

7/ "**Condition of Work**" means the entire field of labor relations between workers and employers including hours of work, wage, leave, payments due to dismissal, workers health and safety, compensation to victims of employment injury, dismissal because of redundancy, grievance procedure and any other similar matters;

8/ "**Occupational Accident**'' means any organic injury or functional disorder sustained by a worker as a result of any cause extraneous to the injured worker or any effort he/she makes during or in connection with the performance of their work;

9/ "**Certificate of Occupational Competence**" means a document issued by an authorized organ evidencing that the worker is capable of performing a particular task;

https://ethiodata.et/

፲/ **"የሁለትዮሽ ስምምነት"** ማለት የውጭ ሀገር የሥራ ቅጥር አስመልክቶ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክና በተቀባይ ሀገር መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው፤

፲፩/ **"የመግባቢያ ሰነድ"** ማለት የውጭ ሀገር የሥራ ቅጥርን አስመልክቶ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በተቀባይ ሀገር መንግስት ወይም በተቀባይ ሀገር ከሚገኝ አሠሪ ጋር ወይም በኢትዮጲያ ያለ ሕጋዊ ድርጅት በተቀባይ ሀገር ከሚገኝ አሠሪ ጋር የሚደረግ በሕግ አስገዳጅነት የሌለውና በትብብር የመስራት ፍላጎትን የሚያመለክት የጋራ መግባቢያ ነው፤

፲፪/ **"አግባብ ያለው ባለሥልጣን"** ማለት በክልል የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕጎችን የማስፈጸም ኃላፊነት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፫/ **"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ መሰረት የተመሰረተ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፲፬/ **"ሚሲዮን"** ማለት በውጭ ሀገር የሚገኝ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን፣ ቋሚ መልዕክተኛ ጽሕፈት ቤት፣ ቆንስላ ጽሕፈት ቤት ወይም የንግድ ጽሕፈት ቤት ነው፤

፲፭/ **"ንግድ ማኅበር"** ማለት የሽርክና ማኅበር፣ የአክሲዮን ማኅበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ነው፤

10/ "**Bilateral Agreement**" means an agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the receiving country pertaining to overseas employment;

11/ "**Memorandum of Understanding**" means an agreement concluded between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia with receiving country or with employer located in receiving country, or between a legal agency in Ethiopia with an employer in receiving country, pertaining to overseas employment;

12/ "**Appropriate Authority**" means a Regional Government organ entrusted with the power to implement labor laws;

13/ "**Region**" means any Regional State specified under Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations;

14/ "**Mission**" means Ethiopia's diplomatic mission, permanent mission, consular office or trade office abroad;

15/ "**Business Organization**" means a partnership, Share Company or Private Limited Company;

https://ethiodata.et/

፲፮/ "**ሌበር አታሼ**" ማለት ሚኒስቴሩ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመመካከር በተቀባይ ሀገር ተመድቦ ለሥራ የተሰማሩ ዜጎችን መብት፣ ደህንነት እና ክብር ተጠብቆ እንዲሰሩ የሚከታተልና ድጋፍ የሚሰጥ ሠራተኛ ነው፤

፲፯/ "**የሰለጠነ የሰው ኃይል**" ማለት ሥራው የሚጠይቀውን ሙያዊ እውቀት እና ክህሎት ከመደበኛ ትምህርት እና ከስልጠና ያገኘ ባለሙያ ነው፤

፲፰/ "**በከፊል የሰለጠነ የሰው ኃይል**" ማለት ሥራው የሚጥይቀውን መስፈርት በከፊል የትምህርት ዝግጅት፣ በልምድ ወይም በስልጠና ያገኘ ባለሙያ ነው፤

፲፱/ "**ባህረኛ**" ማለት በሐመር ላይ ተቀጥሮ ወይም ተመድቦ እንዲሠራ የተደረገ ማንኛውም ሰው ሲሆን አዛዥን እና ለማጆችን ይጨምራል፤

፳/ "**የቤት ውስጥ ሥራ**" ማለት ለትርፍ በሚካሄድ ሥራ ላይ ላልተመሰረተ ሥራ ሆኖ ለአሠሪው እና ለቤተሰብ ፍጆታ የሚውል በቤት ውስጥ የሚሰራ ሥራ ሲሆን እንደ ምግብ ዝግጅት፣ ጽዳት፣ ሞግዚነት፣ የጥበቃ ሥራ፣ ሹፌርነት፣ አትክልተኝነት እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፤

፳፩/ "**የአንድ ማዕከል አገልግሎት**" ማለት ዜጎች ለውጭ ሀገር የሥራ ስምሪትን የሚመዘገቡበት እና ተያይዥ አገልግሎት የሚያገኙበት ማዕከል ነው፤

16/ "**Labor Attaché**" means an officer assigned by the Ministry, in consultation with the Ministry of Foreign Affairs, to a receiving country, whose duty is to monitor and provide support to ensure the protection of the rights, safety and dignity of Ethiopians employed overseas;

17/ "**Skilled Labor**" means an individual who has acquired the knowledge and skills required for the job through formal education or training;

18/ "**Semi-skilled Labor**" means individual who as acquired the knowledge and skills required for the work partly through limited formal education, through experience, or training;

19/ "**Seafarer**" means any person employed or assigned to work on a vessel, including the commander and crew members;

20/ "**Domestic Work**" means a work which does not target profit but is meant for household consumption of the employer and their families, and depending on circumstances, it includes cooking, cleaning, babysitting, security, driving, gardening, and other similar tasks;

21/ "**One Stop Service**" refers to a center where citizens register for overseas employment and receive related services;

https://ethiodata.et/

፳፪/ "**ድንገተኛ አደጋ ምላሽ ሥርዓት**" ማለት በውጭ ሀገር ለሥራ የተሰማሩ ዜጎች ድንገተኛ የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋ፣ ወረርሺኝ ወይም መሰል ሁኔታዎች ተከትሎ ዜጎች በብዛት ወደ ሀገር መመለስ ሲያስፈልግ ሥራ ላይ የሚውል ሥርዓት ነው፤

፳፫/ "**የክህሎት ሥልጠና**" ማለት ዜጎች በሥራ ገበያ ውስጥ ብቁ እና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያስችሉ እውቀቶችን ለማስጠበቅ ከዚህ ቀደም በመደበኛ ወይም በኢ-መደበኛ መንገድ የቀሰሟቸውን የቀደሙ እውቀቶችን እና ክህሎቶችን የሚያዳብሩበት እና ለሚሰማሩባቸው የስራ ዘርፎች የሚወስዷቸውን ሥልጠናዎች ናቸው፤

፳፬/ "**በአጋርነት የሚሰጥ ስልጠና**" ማለት ከውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት ጋር በተያያዘ መንግስት ከመንግስት ፣ መንግስት ከግሉ ዘርፍ ወይም የግል ዘርፍ ከግል ዘርፍ ጋር በመሆን በትብብር የሚሰጥ ስልጠና ነው፤

፳፭/ "**የኤጀንሲ ማኅበራት**" ማለት ቁጥራቸው ከሦስት መቶ በላይ የሆኑ ኤጀንሲዎች የሚያቋቁሙት ማኅበር ነው፤

፳፮/ "**የኤጀንሲዎች ፌዴሬሽን**" ማለት የኤጀንሲዎች ማኅበራት የሚያቋቁሙት ፌዴሬሽን ነው፤

፳፯/ "**የሥራ ውል**" ማለት በአሰሪ እና በሠራተኛ መካከል በጽሁፍ የሚደረግ ስምምነት ነው፤

22/ "**Emergency Response System**" refers to a system established to repatriate in large numbers citizens deployed for overseas employment in response to emergencies arising from natural disaster, man-made accidents, epidemics, or other related emergency circumstances;

23/ "**Skills Training**" refers to the training citizens undertake to gain new, or enhance prior knowledge and skills, acquired formally or non-formally, enabling them to be competent and competitive for their intended job in the labor market;

24/ "**Partnership Training**" means training in relation to overseas employment provided collaboratively by Government with another government, Government with the private sector, or the private sector with private sector;

25/ "**Association of Agencies**" means an association established by more than three hundred agencies;

26/ "**Federation of Agencies**" means a federation formed by agency associations;

27/ "**Contract of Employment**" means a written agreement between an employer and a worker;

https://ethiodata.et/

፳፰/ "**የኮሚሽን ድርድር**" ማለት ሚኒስቴሩ አጥንቶ በሚሰጠው ፈቃድ መሰረት የኤጀንሲዎች ፌዴሬሽን ከመዳረሻ ሀገራት ማህበር ወይም ፌዴሬሽን ወይም ኮንፌዴሬሽን ወይም ከቀጣሪ ድርጅት ወይም ከቀጣሪ ግለሰብ ጋር ለአገልግሎት ክፍያ የሚደረግ ድርድር ወይም ስምምነት ነው፤

፳፱/ "**ሰው**" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፴/ በወንድ ጾታ የተገለጸው ማንኛውም አገላለፅ ሴትንም ይጨምራል፡፡

### ፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ ፦

ኢትዮጵያዊያንን በውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት ለማሰማራት በመንግሥታዊ አካል፣ በኤጀንሲ፣ወይም በቀጥታ በሚደረግ የሥራ ስምሪት እና ግንኙነት ላይ በሚሳተፉ ማንኛውም አካላት ወይም ሠራተኞች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት
## የሥራ ስምሪት አገልግሎት አሰጣጥ እና ኃላፊነት

## ንዑስ ክፍል አንድ

## ስለሥራ ስምሪት አገልግሎት አሰጣጥ

### ፬. የሚኒስቴሩ ተግባርና ኃላፊነት

በዚህ አዋጅ እና በሌሎች ሕጎች ለሚኒስቴሩ የተሰጡት ተግባር እና ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው ሚኒስቴሩ የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት አገልግሎት ይሰጣል፣ ይመራል፣ ያስፈጽማል፣ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ይቆጣጠራል፣ እንደአስፈላጊነቱም ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል።

28/ "**Commission Negotiation**" means a negotiation or agreement concerning service fees, undertaken by the Federation of Agencies with an association or federation or confederation or an employer organization or an individual employer of a destination country, based on the Ministry's research-informed authorization;

29/ "**Person**" means any natural or juridical person;

30 /Any expression to the masculine gender includes the feminine.

### 3. <u>Scope of Application</u>

This Proclamation shall apply to overseas employment relation of Ethiopians conducted by public employment organs, through Agency or by way of direct employment assignment.

## PART TWO

## EMPLOYMENT SERVICE DELIVERY AND RESPONSIBILITIES

## SUB-SECTION ONE

## EMPLOYMENT SERVICE

### 4. <u>Duties and Responsibilities of the Ministry</u>

Without prejudice to the duties and responsibilities granted to the Ministry by this Proclamation and other applicable laws, the Ministry shall provide, lead, execute, coordinate, follow up, and regulate overseas employment services, making appropriate decisions as deemed necessary.

https://ethiodata.et/

## ፭. ስለ ኢትዮጵያ የሥራ ገበያ መረጃ ስርዓት

፩/ በዚህ አዋጅ የኢትዮጵያ የሥራ ገበያ መረጃ ሥርዓት ለውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት የሚሰበሰቡ የሠራተኞች የግል መረጃን፣ የሥራ ውልን፣ የኤጀንሲዎችን፣ የባለድርሻ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን፣ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ጨምሮ ሁሉንም ከኢትዮጵያ የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ለመሰብሰብ፣ ለማከማቸት፣ ለማስተዳደር እና ለማዘመን የተደራጀ የዲጂታል ሥርዓት ነው።

፪/ ሚኒስቴሩ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት አገልግሎት ለመስጠት የተዘረጋውን የሥራ ገበያ መረጃ ስርዓት ተግባራዊ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣ የሥራ ገበያ መረጃ ስርዓት ቋት ያደራጃል፣ እንዳስፈላጊነቱ ያሻሽላል ወይም አዲስ ስርዓት ያለማል፡፡

፫/ ማንኛውም የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት አገልግሎት በሥራ ገበያ መረጃ ስርዓት ውስጥ ማለፍ እና መረጃው በአግባቡ መያዝ ይኖርበታል፡፡

## ፮. የሠራተኛ ምልመላና ስምሪት አገልግሎት

፩/ ሚኒስቴሩ መንግስት ለመንግስት ወይም መንግስት እውቅና ካለው የውጭ አሠሪ ጋር በሚደረግ ስምምነት ወይም የመግባቢያ ሰነድ መሰረት በተቀባይ ሀገር ለሚገኝ መንግስታዊ ድርጅት ወይም አሠሪ ድርጅት ከአንድ ማዕከል ጀምሮ በተዘረጋው የሥራ መረጃ ገበያ ሥርዓት የሠራተኛ ምልመላ እና ስምሪት አገልግሎት ይሰጣል፡፡

## 5. Ethiopia's Labor Market Information System

1/ In this Proclamation, the Ethiopia's Labor Market Information System is a digital system established for collecting, storing, managing, and updating all data pertaining to overseas employment, including, but not limited to, personal data of employees, employment contracts, particulars of agencies, details of other stakeholder service providers, and submitted grievances.

2/ The Ministry shall implement labor market information system established to offer overseas employment service, follow up its implementation, establish repository for labor market information system and amend it as necessary or develop new system.

3/ Any overseas employment service shall pass through the labor market information system and the information shall be duly registered.

## 6. Recruitment and Deployment of Worker

1/ The Ministry, utilizing the labor market information system linked to one stop centers, may provide worker recruitment and deployment services to governmental organizations or employment agencies in receiving country based on government-to-government agreement, memorandum of understanding with government of a receiving country or with legally established overseas employment agency.

https://ethiodata.et/

፪/ ሚኒስቴሩ የሀገር ውስጥ ድርጅት እውቅና ካለው ቀጣሪ የውጭ ሀገር ድርጅት ጋር በሚደረግ የመግባቢያ ሰነድ መሰረት የሥራ ስምሪቱ የተቀጣሪ ዜጎችን መብት እና ደህንነት የሚጠብቅ ስለመሆኑ መርምሮ ሊፈቅድ ይችላል።

፫/ ኤጀንሲ በመዳረሻ ሀገር ከሚገኝ አሠሪ ጋር በሚኖረው እና ሚኒስቴሩ በሚያጸድቀው የሥራ ትዕዛዝ መሰረት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ (፩) አግባብ የተመደበለትን ሠራተኛ ለአሠሪ ያቀርባል፡፡

፬/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሰረት ከሚኒስቴሩ የአሠሪና ሠራተኛ የማገናኘት አገልግሎት ፍቃድ ሳይሰጠው በሌሎች ተቋማት ለንግድ ሥራ ወይም ለሌላ ዓላማ የተሰጠውን ፈቃድ በመጠቀም ለውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት የሠራተኛ ምልመላ ወይም ስምሪት አገልግሎት መስጠት የተከለከለ ነው፡፡

፭/ የባህረኞችን ምልመላ እና ስምሪትን በተመለከተ ሠራተኛው የሚሄድበት ሀገር የዓለም አቀፍ የማሪታይም የአሠሪ እና ሠራተኛ ጉዳይ ኮንቬንሽን አባል ሀገር መሆኑ ሲረጋገጥ ነው።

## ፯. የሠራተኞች ምደባ

፩/ ሚኒስቴሩ ስልጠና የወሰዱ እና ብቃታቸው የተረጋገጠ ሠራተኞችን ኤጀንሲዎች በሚያቀርቡት የሥራ ትዕዛዝ መሰረት ለኤጀንሲዎች ይመድባል።

2/ The Ministry may approve overseas employment arrangements entered, based on memorandum of understanding, between local employment agency and an accredited overseas employment agency upon examining that the employment arrangement respect the rights and safety of the employees.

3/ An agency shall provide an employer with a worker assigned to it in accordance with Article 7 (1) of this Proclamation, based on an agreement with an employer in a destination country and a job order approved by the ministry.

4/ No one can undertake overseas employment and recruitment service using any commercial license or licenses issued for other purpose unless licensed as overseas employment agent by the Ministry according to provisions of this proclamation.

5/ For recruitment and deployment of seafarers, it should be confirmed that the destination country is a member of the international maritime labor affairs convention.

## 7. Placement of Workers

1/ The Ministry shall, upon job order from agencies, do the placement of trained and certified workers to the agencies.

https://ethiodata.et/

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው ቢኖርም ሚኒስቴሩ እንደአስፈላጊነቱ ሠራተኞችን ለማሰማራት በጥናት ላይ የተመሰረቱ ሌሎች አማራጮችን ሊወስድ ይችላል።

፫/ ሚኒስቴሩ ለኤጀንሲዎች የሚያደርገውን የሠራተኛ ምደባን በተመለከተ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ያወጣል፡፡

**፰. <u>ቀጥታ ቅጥር የተከለከለ ስለመሆኑ</u>**

፩/ ማንኛውም አሠሪ በመንግስት ወይም በኤጀንሲ በኩል ካልሆነ በስተቀር በቀጥታ ሠራተኛን መልምሎ ሊቀጥር አይችልም፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ሚኒስቴሩ በሚከተሉት ሁኔታዎች ቀጥታ ቅጥርን ይፈቅዳል፡-

ሀ) አሠሪው የኢትዮጵያ ሚሲዮን አባል ከሆነ፤

ለ) አሠሪው ዓለም አቀፍ ድርጅት ከሆነ፤

ሐ) በግል ጥረት በውጭ ሀገር ለሚገኝ ሥራ ሆኖ ባህርኞችን ይጨምራል ፤

፫/ ማንኛውም የሰለጠነ ወይም በከፊል የሰለጠነ ዜጋ በግል ጥረት በውጭ ሀገር ለሚያገኘው የሥራ ዕድል ሚኒስቴሩ የሥራ ስምሪቱን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) መሰረት መርምሮ መስፈርቱ ከተሟላ የሥራ ስምሪቱን ይፈቅዳል።

፬/ ከግል ጥረት ከሚገኝ ሥራ ዉጪ በመንግስት በኩል የሚደረግ ቀጥታ ቅጥር እንዲፈጸም ለተፈቀደ ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ ሊወጣ የሚችለው በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው ባለስልጣን በኩል ብቻ ነው።

2/ Notwithstanding provisions of Sub-Article (1) of this Article, the Ministry may, based on research, take other courses of action as it deems fit.

3/ The Ministry shall issue a detailed implementation Directive regarding the placement of workers to agencies.

**8. <u>Prohibition of Direct Employment</u>**

1/ No employer shall directly recruit and employ a worker except through government or an agency.

2/ Notwithstanding provisions of Sub-Article (1) of this Article, the Ministry may permit direct employment on the following grounds:

a) where the employer is a staff of an Ethiopian Mission;

b) where the employer is an international organization; or

c) where the job seeker acquires a job opportunity by his own effort, including for seafarers;

3/ Any skilled or semi-skilled citizen who secures an overseas employment opportunity through his personal effort may have his employment permitted by the Ministry, provided it meets requirements set out in Sub-Article (6) of this Article.

4/ Except for overseas employment opportunity through personal effort, vacancy for direct employment initiated by government for recognized overseas employment positions may be advertised only through the Ministry or through such other relevant authority.

https://ethiodata.et/

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት በቀጥታ የሚደረግ ቅጥር በሚኒስቴሩ ሊፈቀድ የሚችለው፦

ሀ) ሠራተኛው በሚሄድበት ሀገር መብቱ፣ ደህንነቱና ክብሩ ሊጠበቅ እንደሚችል ሚኒስቴር ከሚመለከተው ሚሲዮን ወይም በተቀባዩ ሀገር ሚሲዮን ከሌለ ኢትዮጲያ ከሚገኘው የተቀባዩ ሀገር ሚሲዮን ወይም በሌሎች ዘዴዎች በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአሠሪው ሕጋዊነት እና ተያያዥ ጉዳይ ሲረጋገጥ፣

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፷፮ (፩) መሠረት የተገባ የሕይወትና የአካል ጉዳት ካሣ ኢንሹራንስ ሽፋን ስለመኖሩ፤ እና

ሐ) ከሥራ ውሉ ጋር ምቹ የሆነ የመጓጓዣ አገልግሎት የሚያገኝ ስለመሆኑ ማስረጃ ሲቀርብ ብቻ ነው፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## ስለአገልግሎት ሰጪ ተቋማት

### ፱. አንድ ማዕከል አገልግሎት

አንድ ማዕከል አገልግሎት ለውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ለመሰማራት ለሚፈልጉ ዜጎች ምዝገባ እና ተያያዥ አገልግሎቶችን ያከናውናል።

5/ Direct employment under Sub-Article (4) of this Article may be permitted by the Ministry only when:

a) the Ministry confirms from the relevant mission in the destination country or through the receiving country's mission in Ethiopia (if there is no mission abroad), or by other means, that the employer's legality and related issues are confirmed by the Ministry of Foreign Affairs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia as to the worker's rights, safety, and dignity can be protected in the destination country,

b) life and bodily injury compensation insurance coverage is in place, according to Article 66 (1) of this Proclamation;and

c) evidence is presented, along with the employment contract, that the worker will receive convenient transportation services.

## SUB-SECTION TWO
## SERVICE GIVING ORGANIZATIONS

### 9. One Stop Service Center

One-Stop Service Center shall register citizens seeking overseas employment and provide related services.

https://ethiodata.et/

**፲. የክህሎት ልማት ማሰልጠኛ ተቋማት**

፩/ የመንግስት የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት እና ፈቃድ ያላቸው የግል ማሰልጠኛ ተቋማት ወደ ውጭ ሀገር ለሥራ ለሚሰማሩ ዜጎች የክህሎት ስልጠና ይሰጣሉ፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ የክህሎት ልማት ስልጠና ሂደቱን ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል እንደአግባቡ ከማሰልጠኛ ተቋማት ጋር የመረጃ ልውውጥ ስርዓትን ይዘረጋል አፈጻጸሙንም ይከታተላል፡፡

፫/ ሚኒስቴሩ እንደ አስፈላጊነቱ የክህሎት ልማት ስልጠናን አግባብነት ካላቸው አጋር አካላት ጋር በትብብር ሊሰጥ ይችላል፡፡

፬/ ሚኒስቴሩ ለስልጠናው የሚያስፈልግ ክፍያን በተመለከተ በጥናት ላይ በመመስረት ይወስናል አስፈላጊውን ክለሳም ያደርጋል፡፡

፭/ ወደ ውጪ ሀገር ለሥራ የሚሄዱ ሠራተኞችን የክህሎት ሠልጣኞች ምዘናን አስመልክቶ ሚኒስቴሩ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

**፲፩. የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላት**

፩/ የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከል የክህሎት ስልጠና ያጠናቀቁ ዜጎችን በወቅቱ ይመዝናል፤ብቃታቸው እንደተረጋገጠ በተዘረጋው የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ያሳውቃል፡፡

፪/ በማንኛውም ሁኔታ የተገኘ ዕውቀትን እና ክህሎትን ይመዝናል ብቁ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

**10. Skills Development Training Centers**

1/ Public technical and vocational education and training institutions and licensed private training institutions shall offer skills development training for citizens pursuing overseas employment.

2/ The Ministry shall support, follow up and monitor the skills development training process and establish an information exchange system with training institutions and follows up its implementation.

3/ As it deems necessary, the Ministry may offer the skills development trainings in cooperation with pertinent stakeholders.

4/ The Ministry shall determine training fees based on study and make any necessary revisions thereto.

5/ The ministry shall issue a detailed Directive regarding the assessments of workers' skills for overseas employment.

**11. Occupational Competency Assessment Centers**

1/ An occupational competency assessment center shall timely assess citizens who have completed the skills development training; once their competency is confirmed, shall notify their competence level through the established information exchange system.

2/ It shall assess knowledge and skills acquired through any means and ensure competencies thereto.

https://ethiodata.et/

፫/ ሚኒስቴሩ ከሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላት ጋር የመረጃ ልውውጥ ስርዓትን ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል።

## ንዑስ ክፍል ሦስት
## በውጭ አገር ሥራ መሰማራት ስለሚያስችሉ የክህሎት ዓይነቶች

**፲፪. የሰለጠነ የሰው ኃይል**

በውጭ ሀገር ሥራ ላይ ሊሰማራ የሚችለው:-

፩/ የሥራ መደቡ የሚጠይቀውን የትምህርት ዝግጅት፣ ከፍተኛ የዘርፍ እውቀት የሙያና የሥራ ልምድ የሚያሟላ ሲሆን፤ እና

፪/ በሚቀጠርበት የሥራ መስክ አግባብ ካለው የምዘና ማዕከል የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ያለው መሆን አለበት፡፡

**፲፫. በከፊል የሰለጠነ የሰው ኃይል**

በውጭ ሀገር ሥራ ላይ ሊሰማራ የሚችለው:-

፩/ የሥራ መደቡ የሚጠይቀውን የትምህርት ዝግጅት በከፊል የሚያሟላ፣ ከፊል የዘርፍ እውቀት በትምህርት ወይም በልምድ ያለው እና የሚሰማራበት የሥራ መደብ ከፍተኛ የሙያ ክህሎት የማይጠይቅ ሲሆን ወይም፣

፪/ በሚቀጠርበት የሥራ መስክ አግባብ ካለው የምዘና ማዕከል የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ያለው መሆን አለበት፡፡

**፲፬. በልምድ የተገኘ ክህሎት ያለው የሰው ኃይል**

በውጭ ሀገር ሥራ ላይ ሊሰማራ የሚችለው :-

፩/ ሠራተኛው የትምህርት ዝግጅት ባይኖረውም በልምድ የተገኘ እውቀት እና ክህሎት ኖሮት የሥራ መደቡ የትምህርት ዝግጅት የማይጠይቅ እና ሥራው ተደጋጋሚ እንዲሁም በአመዛኙ የሠራተኛውን ጉልበት የሚጠይቅ ሲሆን እና፣

3/ The Ministry shall establish information exchange system with occupational competence assessment centers and supervise the implementation thereof.

## SUB-SECTION THREE
## TYPES OF SKILLS ENABLING OVERSEAS EMPLOYEMENT

**12. A skilled worker**

May be employed in an overseas job if he:

1/ Possesses the educational qualifications, specialized sectoral knowledge and skills, and relevant professional and work experience required by the position;

2/ Holds an occupational competency certification from an accredited assessment center as deemed necessary for the targeted field of employment.

**13. A semi-skilled worker**

May be employed in an overseas job if he:

1/ Partially meets the educational qualifications required by the position, possesses partial sectoral knowledge and skills gained through education or experience,

2/ Holds an occupational competency certification from an accredited assessment center as deemed necessary for the targeted field of employment.

**14. Experience-based skilled worker**

May be employed in an overseas job if he:

1 / Possesses knowledge and skills acquired through experience provided the position does not require education and involves routine tasks often demanding manual labor and ,

https://ethiodata.et/

፪/ በሚቀጠርበት የሥራ መስክ እንደአስፈላጊነቱ አግባብ ካለው የምዘና ማዕከል የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ያለው መሆን አለበት፡፡

2/ Holds an occupational competency certification from an accredited assessment center as deemed necessary for the targeted field of employment.

**ንዑስ ክፍል አራት**

**ለውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች**

**SUB-SECTION FOUR**

**ELIGIBILITY CRITERIA FOR OVERSEAS EMPLOYEMENT**

**፲፭. ስለ ትምህርት**

ማንኛውም በውጭ ሀገር ለሥራ የሚሰማራ ሠራተኛ የሚቀጠርበት የሥራ መስክ የሚጠይቀውን እውቀት ወይም ክህሎት ያለው እና ቢያንስ በሚረዳው ቋንቋ የሚዘጋጀውን ውል አንብቦ የሚረዳ መሆን ይኖርበታል።

**15. Level of Education**

Any worker undertaking overseas employment shall acquire the knowledge or skills necessary to perform his work and shall at least be able to read and comprehend the contract document prepared in the language he understands.

**፲፮. ስለብቃት**

፩/ ማንኛውም በውጭ ሀገር ለሥራ የሚሰማራ ሠራተኛ በሚቀጠርበት የሥራ መስክ ትምህርት ወይም ስልጠና ወስዶ ወይም በማንኛውም ሁኔታ እውቀትና ክህሎት አግኝቶ አግባብነት ካለው የትምህርት ተቋም ወይም የምዘና ማዕከል የተሰጠ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ መያዝ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሠራተኛ በውጭ ሀገር ሲሰራ ቆይቶ አገሩ የተመለሰ ከሆነ በሚቀጠርበት የሥራ መስክ የክለሳ ስልጠና ወስዶ አግባብ ባለው የምዘና ማዕከል የተሰጠ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ከያዘ ወደ ውጭ ሀገር ሄዶ ለመሥራት ብቁ ይሆናል፡፡

**16. Competency**

1/ Any worker who engages in overseas employment shall possess occupational competency certification issued by a relevant educational institutions or assessment center, proving he has acquired the necessary knowledge and skills for his field of employment through education, training, or any other means.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, any Ethiopian worker who has been working overseas and returned to the country, will be eligible for overseas employment if he takes refresher training and obtains occupational competency certification from the relevant assessment center.

https://ethiodata.et/

፫/ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሠራተኛ በውጭ ሀገር ሲሰራ ቆይቶ ሀገሩ የተመለሰ ከሆነ እና የሚቀጠርበት የሥራ መስክ ቀድሞ ሲሰራው ከነበረው የተለየ ከሆነ እንደአዲስ ስልጠና ወስዶ አግባብ ባለው የምዘና ማዕከል የተሰጠ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ መያዝ ይኖርበታል፡፡

3/ Any Ethiopian worker returning from overseas employment shall obtain occupational competency certification from the relevant assessment center, following new training, if his new field of employment differs from his previous one.

## ፲፯. ስለ ጤና ምርመራ

## 17. Medical Examination

፩/ የሠራተኛ የጤና ምርመራ የሚደረገው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጤና ሚኒስቴር እና እንደአስፈላጊነቱ የመዳረሻ ሀገራት በጋራ በሚመርጡት የጤና ተቋም ብቻ ይሆናል፡፡

1/ Medical examination for worker shall be undertaken exclusively at health institutions jointly selected by the Ministry of Health of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and, as necessary, by countries of destination.

፪/ ሠራተኛ የጤና ምርመራ ማከናወን ያለበት አሠሪው የሚጠይቃቸውን ሌሎች መስፈርቶች ማሟላቱ ሲረጋገጥ ብቻ ይሆናል፡፡

2/ Medical examination shall be undertaken only when it is ascertained that the worker fulfills other requirements of the employer.

፫/ ሚኒስቴሩ የጤና ተቋማት የሚመረጡበትን አግባብ እና የጤና ምርመራ ሂደቱን በተመለከተ ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ያወጣል፡፡

3/ The Ministry in collaboration with the Ministry of Health shall issue detailed implementation Directive concerning the selection of health facilities and the health examination process.

## ፲፰. የጉዞ ሰነዶች

## 18. Travel Documents

ለውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት ጉዞ የሚያስፈልጉትን ሰነዶችን እንደጉዳዩ አግባብነት በኤጀንሲው ወይም በሠራተኛው ለሚኒስቴሩ ይቀርባሉ፤ ሚኒስቴሩም እንደአስፈላጊነቱ እነዚህ የጉዞ እና ተያይዥ ሰነዶች እንዲሟሉ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፡፡

Travel documents required for overseas employment shall be presented to the Ministry by the agency or the worker, as appropriate, and the Ministry shall collaborate with relevant bodies, as needed, to ensure these travel and related documents are complete.

https://ethiodata.et/

## ንዑስ ክፍል አምስት

## ስለወጪ አሸፋፈንና የአገልግሎት ክፍያ

**፲፱. ስለወጪ አሸፋፈን**

፩/ የሚከተሉት ወጪዎች በአሠሪው ይሸፈናሉ፡-

ሀ/ የተቀባይ ሀገር የመግቢያ ቪዛ ክፍያ፤

ለ) የደርሶ መልስ የመጓጓዣ ክፍያ፤

ሐ) የሕክምና ምርመራ እና ክትባት ወጪ፤

መ/ የሥራ ፈቃድ ክፍያ፤

ሠ/ የመኖሪያ ፈቃድ ክፍያ፤

ረ) የሠራተኛ የመድህን ዋስትና ሽፋን፤

ሰ/ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኝ ለተቀባይ ሀገር ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጽሕፈት ቤት የሚከፈል ከቪዛና ከሰነድ ማረጋገጥ ጋር የተያያዘ ማንኛውንም ወጪ፤ እና

ሸ/ የሥራ ውል ማፅደቂያ የአገልግሎት ክፍያ፡፡

፪/ የሚከተሉት ወጪዎች በሠራተኛው ይሸፈናሉ፡-

ሀ) የፓስፖርት ማውጫ ወጪ፤

ለ) ከወንጀል ነጻ ማስረጃ ማረጋገጫ ወጪ፤

ሐ) የልደት ሰርተፊኬት ማውጫ ወጪ፤ እና

መ) የሥልጠና ወጪ፤ እና

ሠ) የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ወጪ፡፡

## SUB-SECTION FIVE

## EXPENSE COVERAGE AND SERVICE FEE

**19. Expense Coverage**

1/ The employer shall cover the following expenses:

a) entry visa fee to the country of destination;

b) round trip transport cost;

c) cost of medical examination and vaccination;

d) work permit fee;

e) residence permit fee;

f) insurance coverage;

g) costs associated with visa and document authentication paid to the embassy of country of destination domiciled in Ethiopia; and,

h) employment contract approval service fee.

2/ The worker shall cover the following expenses:

a) passport issuance fee;

b) cost of criminal record clearance;

c) birth certificate issuance fee;

d) cost of training ; and

e) expense for certificate of occupational competence.

https://ethiodata.et/

፫/ ሠራተኛው በግል ጥረት ወይም በትብብር እና በአጋርነት ወይም የሰለጠነ የሰው ሃይል ሲሆን ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ከተመለከተው ውጪ በሌላ አግባብነት ባለው ሁኔታ ለሚገኘው የውጭ ሀገር ስምሪት አገልግሎት ወጪ በአሰሪው እና በሰራተኛው በሚኖር ስምምነት መሰረት በሚንስቴሩ ፍቃድ የሚፈጸም ይሆናል።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከቱ ወጪዎችን ሠራተኛው አውጥቶ በአሰሪው ወይም በኤጀንሲው ጉድለት ምክንያት በሥራ ላይ ካልተሰማራ ኤጀንሲው ወይም አሠሪው የሠራተኛውን ወጪ የመተካት ግዴታ ይኖርበታል፡፡

፭/ ለሥራ ወደ ውጭ ሀገር ለመሄድ አስፈላጊ ሁኔታዎች ተጠናቀው ያለበቂ ምክንያት ሠራተኛው ወደ ሥራው ባይሰማራ ከቅጥሩ ጋር በተያያዘ አሠሪው በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) ያወጣውን ወጪ ሠራተኛው እንዲከፍለው ሊጠይቅ ይችላል፡፡

**፳. <u>የአገልግሎት ክፍያ</u>**

ሚኒስቴሩ የሥራ ውል ማጽደቂያ ክፍያን፣ የኤጀንሲ ፍቃድ ማውጫ እድሳትን እና የቅጣት እንዲሁም ሌሎች መሰል ክፍያዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት ተፈጻሚ ያደርጋል።

## ንዑስ ክፍል ስድስት

## ስለሁለትዮሽ ስምምነት እና የመግባቢያ ሰነድ

**፳፩. <u>የሁለትዮሽ ስምምነት ወይም የመግባቢያ ሰነድ ስለማስፈለጉ</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት ሠራተኛን በውጭ ሀገር ለሥራ ማሰማራት የሚቻለው:-

3/ For overseas employment secured through personal effort, collaboration and partnership, or as skilled labor, or in any other relevant situation outside of what is stipulated in Sub-Articles (1) and (2) of this Article, the service fee shall be covered based on the agreement entered between the employer and the worker, with the Ministry's approval.

4/ If a worker incurs the expenses mentioned in Sub-Article (2) of this Article but is not deployed due to a fault of the employer or agency, then the agency or employer shall be obliged to refund the worker's expenses.

5/ Whenever the worker, without justified cause, fails to be deployed for work after all requirements for departure are fulfilled, the employer may require the worker to refund expenses incurred regarding the employment pursuant to Sub-Article (1) of this Article.

**20. <u>Service Fee</u>**

The Ministry shall charge the employer a service fee associated with the approval of contract of employment, renewal and penalty as well as such other expenses, in accordance with Regulations issued by the Council of Ministers.

## SUB-SECTION SIX

## BILATERAL AGREEMENTS AND MEMORANDUM OF UNDERSTANDING

**21. <u>Requirements of Bilateral Agreement or Memorandum of Understanding</u>**

1/ Deployment of workers for overseas employment in accordance with this Proclamation shall be effected:

https://ethiodata.et/

ሀ) እንደአግባቡ በኢትዮጵያ መንግስት እና በተቀባይ ሀገር መንግስት መካከል የሁለትዮሽ የሥራ ስምሪት ስምምነት ወይም መግባቢያ ሰነድ ሲኖር ወይም በሚኒስቴሩ እና በተቀባይ ሀገር ከሚገኝ አቻ ሥልጣን ካለው የመንግስት ተቋም ወይም እውቅና ካለው አካል የሁለትዮሽ ስምምነት ወይም መግባቢያ ሰነድ ሲኖር፤

ለ) በንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) የተጠቀሰው ቢኖርም የባህረኞች የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፤

ሐ) ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሠለጠነ የሰው ኃይል የሚሰማራበትን ሥራ አፈላልጎ ያገኘ ኤጀንሲ በዚህ አዋጅ የተቀመጠው የኤጀንሲዎች ደረጃ በሚፈቅድለት አግባባ የሥራ ስምሪት ስምምነት እንዲፈፅም ሚኒስቴሩ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተገለጸው ቢኖርም በግል ጥረት ለሚገኝ ሥራ ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ ፲፭ እስከ አንቀጽ ፲፰ ላይ የተቀመጡትን ቅድመ ሁኔታዎችን ብቻ መሟላታቸውን አረጋግጦ ሊፈቅድ ይችላል።

**፳፪. ሌበር አታሼ ስለመመደብ**

፩/ ሚኒስቴሩ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመመካከር በውጭ ሀገር ለሥራ የሚሰማሩ ዜጎች መብት፣ ደህንነት እና ክብር እንዲጠበቅ ሌበር አታሼ በተቀባይ ሀገር በሚገኘው ሚሲዮን ይመድባል።

a) when there is bilateral labor agreement or memorandum of understanding concluded between the Government of Ethiopia and the government of the receiving country, or when there is memorandum of understanding or bilateral labor agreement concluded between the Ministry and equivalent government authority or accredited employing company in the receiving country;

b) without prejudice to the provisions of Sub-Article (1) paragraph (a) above, this shall not apply to overseas employment of seafarers;

c) Notwithstanding the provisions of this Sub-Article (1) paragraph (a) and (b) , the Ministry may permit an agency that has found employment for skilled labor to enter into an employment agreement in accordance with the agency's classification level as stipulated in this Proclamation.

2/ Without prejudice to provisions of Sub-Article (1) of this Article, the Ministry may grant permission for employment secured through personal effort upon confirming that the preconditions stated in Articles (15) and (18) of this Proclamation are met.

**22. Assignment of Labor Attaché**

1/ The Ministry, in consultation with the Ministry of Foreign Affairs, shall assign Labor Attaché to the mission in the receiving country to ensure the rights, safety and dignity of workers employed overseas are protected.

https://ethiodata.et/

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ሚኒስቴሩ ሚሲዮን በሌለባቸው ተቀባይ ሀገራት ሌበር አታሼ የሚመደብበትን ወይም የሌበር አታሼ ሥራ የሚሰራበትን ሁኔታ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመነጋገር ወስኖ ተግባራዊ ያደርጋል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚመደበው የሌበር አታሼ ብዛት ተግባርና ኃላፊነት ሚኒስቴሩ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመመካከር በሚያወጡት የአሰራር መመሪያ ይወሰናል፡፡

**፳፫. ቦርድ ስለማቋቋም፣ አባላት እና ስልጣን እና ተግባር**

፩/ የኢትዮጵያ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ቦርድ (ከዚህ በኋላ ቦርድ እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪/ የቦርዱ ዓላማ አግባብነት ያላቸውን ባለድርሻ መሥሪያ ቤቶችን በማስተባበርና በማቀናጀት ወደ ውጭ ሀገር ለሥራ የሚሠማራውን ዜጋ መብቱ፣ ክብሩና ደህንነቱ ተጠብቆ ለሥራ እንዲሠማራ የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት ተጠናክሮ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡

፫/ የቦርዱ አባላት፡-

የቦርዱ ሰብሳቢ በጠቅላይ ሚኒስቴሩ የሚሰየም ሆኖ አባላቱ ከሚከተሉት ተቋማት ይሆናሉ፡-

ሀ) ሥራና ክህሎት ሚኒስቴር (ጸሐፊ)

ለ) የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፤

ሐ)የጤና ሚኒስቴር፤

መ)የፍትህ ሚኒስቴር፤

ሠ)የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን፤

2/ Notwithstanding provisions of Sub-Article (1) of this Article, the Ministry, in consultation with the Ministry of Foreign Affairs, shall decide and implement the assignment of labor attaché to receiving countries where there is no Ethiopian mission, or how the duties of a labor attaché will be carried out in such places.

3/ The number, duties and responsibilities of the labor attaché to be assigned pursuant to Sub-Article (1) of this Article shall be determined by an operational Directive consultatively issued by the Ministry and the Ministry of Foreign Affairs.

**23. Establishment of Board, its Members, and Powers and Duties**

1/ Ethiopian Overseas Employment Board (hereinafter Board) is hereby established under this Proclamation.

2/ The objective of the Board is to coordinate relevant stakeholders towards strengthening the implementation of overseas employment and ensuring that the rights, safety and dignities of Ethiopians employed overseas are protected.

3/ Members of the Board:

While the chair is appointed by the Prime Minister, the board will have the following institutions as its members:

a) Ministry of Labor and Skills shall be the Secretary of the board;

b) Ministry of Foreign Affairs;

c) Ministry of Health;

d) Ministry of Justice;

e) Federal Police Commission;

https://ethiodata.et/

ረ) የኢሚግሬሽን እና የዜግነት አገልግሎት፣
ሰ) ብሔራዊ ባንክ፣
ሸ) የኤጀንሲዎች ፌዴሬሽን፣
ቀ) የፋይናንስ ደኅንነት አገልግሎት፣
በ) ብሔራዊ መረጃ ደህንነት አገልግሎት፣
ተ) የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣
ቸ) ሌሎች አግባብነት ያላቸው ተቋማት እንደአስፈሊጊነቱ የሚካተቱ ይሆናል፡፡

፬/ የቦርዱ ሥልጣን እና ተግባር እንደሚከተሉ ይሆናል፡-

ሀ) አዋጁ ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ያረጋግጣል፣
ለ) ከውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ከተቀባይ ሀገራት ጋር ስምምነት ወይም የመግባቢያ ሰነድ የሚደረግበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣
ሐ) ለሥራ ወደ ውጭ ሀገር የተሰማሩ ዜጎችን መብት ክብር ጥቅም እና ደህንነት መጠበቁን ያረጋግጣል፣
መ) በተቀባይ ሀገር በዜጎች ላይ የመብት መጣስ ወይም ጉዳት ሲደርስ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አስፈሊጊውን እርምጃ መወሰዱን ያረጋግጣል፣
ሠ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በሕገ- ወጥ ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ድርጊት የሚሳተፉ አካላት ላይ በሕግ አግባብ ተገቢው እርምጃ መወሰዱን ያረጋግጣል፣

f) Immigration and Citizenship Service;
g) National Bank of Ethiopia;
h) Federation of Agencies;
i) Financial Intelligence Service;
j) National Intelligence and Security Service ;
k) Ethiopian Airlines ;
i) Other relevant institutions may be included as deemed appropriate.

4/ Powers and Duties of the Board:

a) follows up, supervise and ensure the proper implementation of this Proclamat ion;
b) facilitates the conclusion of bilateral agreement or memorandum of understanding with receiving countries and follow up implementation;
c) ensures that the rights, dignities and interests of citizens involved in overseas employment are respected;
d) ensures that necessary action is taken, in collaboration with relevant authorities, when rights violations or harm occur to Ethiopian workers in receiving countries;
e) ensures that appropriate legal action is taken against entities involved in illegal overseas employment and worker recruitment activities;

https://ethiodata.et/

ረ) የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪትን በተመለከተ አግባብነት ካላቸው አካላት እና አደረጃጀት ጋር በትብብር ይሰራል የተጠናከረ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

ሰ) የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት በተመለከተ ለሕብረተሰቡ ግንዛቤ መፈጠሩን ያረጋግጣል፤

ሸ) ሕጋዊ የውጪ ሀገር የሥራ ስምሪትን ለማበረታታት የሚያስችል አቅጣጫ ለተቋማት ያስቀምጣል፤ የተቀመጠው አቅጣጫ በተቋማት ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል እንዲሁም ያረጋግጣል፤

ቀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፩ (፬) ላይ ኢትዮጵያዊ፣ ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወይም የውጭ ሀገር ዜጋ ኤጀንሲ አቋቁመው ለመሥራት ስለሚኖራችው የገንዘብ መዋጮ ሊቀንስ ወይም ሊጨምር ይችላል፤

በ) የራሱን የውስጥ አደረጃጀት እና አሰራር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

## ፳፬. የኤጀንሲዎች ማኅበራት እና ፌደሬሽን

፩/ በውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት ላይ የሚሳተፉ ከሶስት መቶ በላይ ኤጀንሲዎች ማህበር ሊያቋቁሙ ይችላሉ።

፪/ የኤጀንሲ ማህበራት ፌዴሬሽን ሊያቋቁሙ ይችላሉ።

፫/ የኤጀንሲ ፌዴሬሽን በዚህ አዋጅ የሚከተሉት ተግባር እና ኋላፊነት ይኖርበታል፡-

ሀ) አዋጁን እና አዋጁን ተከትለው የወጡ ደንብ እና መመሪያ የመፈጸም እና የማስፈጸም፤

f) collaborates with relevant stakeholders and organizations in relation to overseas employment and facilitates conditions for information exchange;

g) ensures public awareness is created concerning overseas employment;

h) sets directions for institutions pertaining to promoting legal overseas employment; follows up, supervises and ensures the implementation of these directions by institutions;

i) may reduce or increase contributions of Ethiopians, people of Ethiopian origin and foreign citizens seeking to establish an agency, as provided in Article 31(4) of this proclamation;

k) issues its own internal structure and operational Directives.

## 24. Agency Associations and Federation

1/Three hundred agencies involved in overseas employment can establish an association.

2/ Associations of agencies can establish a federation.

3/ The Agency Federation shall have the following duties and responsibilities under this Proclamation:

a) implement and cause implementation of this Proclamation as well as Regulations and Directives which follows the proclamation;

https://ethiodata.et/

ለ) ከውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት ጋር በተያያዘ የተከናወኑን ተግባራትን ላይ ለሚኒስቴሩ በየ፫ ወሩ ሪፓርቶችን የማቅረብ፤

ሐ) ሕገ-ወጥ ተግባራት ላይ የሚገኙ ኤጀንሲዎችን እና ማኅበራትን ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ለሚኒስቴሩ ዝርዝር ሪፖርት የማቅረብ፤

መ) ከመዳረሻ አገራት ኤጀንሲዎች ወይም ማኅበራት ጋር የሚደረግ ማንኛውም የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪትን የተመለከቱ ስምምነቶች እና የኮሚሽን ድርድር ውጤቶችን ለሚኒስቴሩ ያሳውቃል፤

ሠ) በውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት ቦርድ ውስጥ ኤጀንሲዎችን ይወክላል፤

ረ) ሚኒስቴሩ ከተቀባይ አገራት ጋር በሚያደርጋቸው የሁለትዮሽ እና መሰል የሥራ ሥምሪት ስምምነቶች ሒደቶች ላይ እንዲሳተፍ ሊያደርገው ይችላል።

፬/ ሚንስቴሩ የኤጀንሲ ማህበራትና ፌድሬሽን ስለሚመለከቱ ጉዳዮች ዝርዝር መመሪያ ያወጣል።

## ፳፭. የተከለከለ ድርጊት

፩/ ከሚኒስቴሩ እውቅና ውጪ ከመዳረሻ ሀገራት ጋር ስምምነት እና የኮሚሽን ድርድር ማድረግ የተከለከለ ነው።

፪/ በንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተቀመጠውን ክልከላ ተላልፎ ድርድር አድርጎ የተገኘ ኤጀንሲ ወይም ማኅበር ፈቃዱ መሰረዙ እንደተጠበቀ ሆኖ የድርድር ውጤቱም ተቀባይነት አይኖርም።

b) submit to the Ministry every three months, a report on activities performed regarding overseas employment;

c) submit detailed report to the Ministry recommending measures to be taken on agencies and associations involved in illegal activities;

d) notify the Ministry of any overseas employment agreements concluded and results of commission negotiations with agencies and associations at destination countries;

e) represent agencies within the Overseas Employment Board;

f) the Ministry may allow it to participate in the process of bilateral agreements and similar employment agreements it undertakes with receiving countries.

4/ The Ministry shall issue detailed Directive concerning agency associations and federations.

## 25. Prohibited Act

1/ It is prohibited to undertake agreement and commission negotiation with countries of destination without the knowledge of the Ministry.

2/ Any agency or association which is found to have undertaken negotiation in violation of the provisions of Sub-Article (1) of this Article will have its license revoked and the outcome of such negotiation will be rendered invalid.

https://ethiodata.et/

## ክፍል ሦስት
## ስለ ሥራ ሁኔታዎች
## ንዑስ ክፍል አንድ
## የሥራ ሁኔታዎችን ስለመወሰን

### ፳፮. ስለ ሞዴል የሥራ ውል ይዘት

፩/ ሚኒስቴሩ ቢያንስ የሚከተሉትን ዝርዝሮች የያዘ ሞዴል የሥራ ውል ያዘጋጃል፦

ሀ) ኢትዮጵያና ተቀባይ ሀገር ባደረጉት የሠራተኛ ቅጥር ሁለትዮሽ ስምምነት መነሻ ክፍያ ተብሎ ከተደረሰው፣ ሁለቱ አገሮች ባፀደቁት ዓለም አቀፍ ስምምነት ከተመለከተው አነስተኛ የደመወዝ መጠን የማያንስ እና የተሻለ ጥቅም የሚሰጥ የደመወዝ፣ መደበኛ የሥራ ሰዓት እና የትርፍ ሰዓት ክፍያ፤

ለ) የዓመት፣ የሣምንት እና የመሳሰሉት ዕረፍቶች፤

ሐ) ወደ ሥራ ቦታ መሄጃና ከሥራ ቦታ መመለሻ ነፃ የትራንስፖርት አገልግሎት ወይም ተመጣጣኝ ክፍያ፤

መ) በስራ ላይ ለሚደርሱ አደጋዎች ነፃ ሕክምና፣ ምግብና መጠለያ ወይም ተመጣጣኝ ክፍያ፤

ሠ) የሕይወትና የአካል ጉዳት ዋስትና ሽፋን፤

ረ) ከውሉ ጋር የተያያዙ አለመግባባቶችን ስለሚፈቱበት ሁኔታ፤

ሰ) የሥራ ውል የሚቋረጥባቸው በቂ ምክንያቶች፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ሞዴል የሥራ ውሉ ሠራተኛው በሚረዳው ቋንቋ፣ በእንግሊዘኛ እና በአሠሪው ቋንቋ ያዘጋጃል።

## PART THREE
## CONDITIONS OF WORK
## SUB SECTION ONE
## DETERMINATION OF CONDITIONS OF WORK

### 26. Content of Model Contract of Employment

1/ The Ministry shall prepare model contract of employment, at least including the following:

a) regular working time, favorable wages for regular working hours and overtime pay, which shall not be lower than the appropriate minimum wage set by the bilateral agreement between Ethiopia and the receiving country, or in the international agreements ratified by both countries;

b) annual leave, weekly rest and other similar vacations;

c) free transportation to and from the worksite or offsetting benefit;

d) free medication, food and accommodation or offsetting benefits for work-related accidents;

e) insurance coverage for life and disability;

f) procedure for resolving disputes related to the contract;

g) valid reasons for termination of employment contract.

2/ The Ministry shall prepare model contract of employment in the working language which the worker understands, in English and in the language of the employer.

https://ethiodata.et/

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ሞዴል የሥራ ውል ሲዘጋጅ በመሠረታዊነት የሚከተሉት መገናዘብ ይኖርባቸል፡-

ሀ) መሰረታዊ የአሰሪና ሰራተኛ ሕጎች እና ፖሊሲዎች፤

ለ) የተቀባይ ሀገር ባህል፣ ልማድ፣ አኗኗር፣ የአሠሪና ሠራተኛ ሕጎች እንዲሁም የአሠሪ ድርጅት ፖሊሲዎች፤

ሐ) ከተቀባይ ሀገር ጋር የተፈረሙ አግባብ ያላቸው የሁለትዮሽ እና የባለ ብዙ ወገን ስምምነቶች፣ የመግባቢያ ሰነዶች፣ ዓለም አቀፍ የቃልኪዳን ሰነዶች ወይም ኮንቬንሽኖች እና ውሳኔዎች፤

መ) የሥራ ገበያው ወቅታዊ ሁኔታዎች፡፡

**፳፯. <u>የተዋዋይ ወገኖች ነፃነት</u>**

ለሠራተኛ ይበልጥ የሚጠቅም እና የኢትዮጵያ የመንግሥት ፖሊሲ፣ ሕግንና የሕብረተሰቡን ሞራል የማይቃረን እስከሆነ ድረስ ተዋዋይ ወገኖች በሞዴል የሥራ ውል ያልተመለከቱ ሌሎች የሥራ ሁኔታዎችንና ጥቅሞችን በሥራ ውላቸው ውስጥ ሊያካትቱ ይችላሉ፡፡

**፳፰. <u>መረጃ የመያዝ ሃላፊነት</u>**

፩/ ማንኛውም በውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት ውስጥ የሚሳተፍ አካል ወይም ኤጀንሲ ከሠራተኛ ምልመላና ቅጥር ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን መረጃዎች እና ስለሠራተኛው ሁኔታ የሚጠየቁ ሌሎች መረጃዎችን ሁሉ አደራጅቶ የመያዝ እና ለሚኒስቴሩ፣ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ወይም ለሚሲዮኑ በሚጠየቅበት ጊዜ ውስጥ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

3/ When a model contract of employment is prepared in accordance with Sub-Article (1) of this Article, the following shall be fundamentally taken into account:

a) fundamental labor laws and policies ;

b) the culture, custom, way of life and the labor and social affairs laws of the receiving country and the policies of the employing enterprise;

c) relevant bilateral and multilateral treaties signed with receiving country, international conventions and resolutions;

d) prevailing labor market conditions.

**27. <u>Freedom of Contracting Parties</u>**

Parties to overseas employment contract are at liberty, without contravening Ethiopian government policies, laws and public morality, to stipulate other terms, conditions and benefits that are not provided for in the model contract if it is more beneficial to the worker than the minimum set in the model contract.

**28. <u>Responsibility to Keep Data</u>**

1/ Any Agency or entity which partakes in overseas employment shall organize and keep data pertaining to worker's recruitment and all other related information requested in relation to conditions of the employee, and shall submit to the Ministry, to other pertinent authority or to the mission whenever such data (information) is required.

https://ethiodata.et/

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት መረጃዎች እንደ አግባብነታቸው ሊቀርቡበት የሚገባውን ጊዜ ሚኒስቴሩ በማስታወቂያ ይወስናል፡፡

፳፱. **<u>የሥራ ሁኔታዎችን ስለመወሰን እና ስለቁጥጥር አገልግሎት</u>**

፩/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለስልጣን ማንኛውም ኤጀንሲ በዚህ አዋጅ መሠረት የተጣለበትን ግዴታና ኃላፊነት እየተወጣ ስለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግ የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት ተቆጣጣሪ ይመድባል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተመደበ ማንኛውም የውጭ ሃገር የሥራ ስምሪት ተቆጣጣሪ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፦

ሀ) ለኤጀንሲ የሥራ ፈቃድ ከመሰጠቱ ወይም ከመታደሱ ወይም ነባሩን የቢሮ አድራሻ ከመለወጡ በፊት የተሟላ ቢሮ እና ባለሙያ መኖሩን የማረጋገጥ፤

ለ) በቴክኖሎጂ የተደገፈ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝና አጠቃቀም ሥርዓት የዘረጋ መሆኑን የማረጋገጥ፤

ሐ) የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን ኤጀንሲው መተላለፉን ራሱ ሲረዳ ወይም ጥቆማ ሲደርሰው ተገቢውን ማጣራት የማከናወን፤

መ) ሕገ ወጥ የሠራተኛ ምልመላና ቅጥር ተግባር እንዳይከናወን ቁጥጥር የማድረግ፤

2/ The Ministry shall determine and notify the appropriate timeframe for submitting information pursuant to Sub-Article (1) of this Article.

29. **<u>Determining Working Conditions and Inspection Services</u>**

1/ The Ministry or appropriate authority shall assign overseas employment inspector who follows up and inspects whether any agency is fulfilling duties and responsibilities under this Proclamation.

2/ Any overseas employment inspector assigned by the Ministry or the appropriate authority pursuant to Sub-Article (1) of this Article shall have the following powers and duties:

a) ascertain prior to licensing the agency or change of existing office, that an Agency has possessed fully equipped office and necessary expertise for conducting the business;

b) ensure that the agency has put in place technology-supported information management and utilization system;

c) undertake appropriate investigation whenever he is aware or is notified that an Agency has contravened provisions of this Proclamation or Regulations or Directives issued hereunder;

d) undertake monitoring so as to prevent illegal recruitment and deployment of workers;

https://ethiodata.et/

ሠ) በኤጀንሲው ቢሮ በማንኛውም የሥራ ሰዓት በመገኘት አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን፣ መዝገቦችን፣ የሂሳብ መዛግብቶችንና የመሳሰሉትን የመመርመርና ጥያቄ የማቅረብ።

፫/ የውጭ ሃገር የሥራ ስምሪት ተቆጣጣሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ቁጥጥር ሲያካሂድ ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ካለው ባለሥልጣን የተሰጠውን መታወቂያ ይዞ መገኘት እና ማሳየት አለበት፤

፬/ የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት ተቆጣጣሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ባካሄደው ቁጥጥር የደረሰበትን ግኝትና ሊወሰድ ስለሚገባው ሕጋዊ እርምጃ ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ለሚመለከተው የሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለሥልጣን የሥራ ሃላፊ ማቅረብ አለበት፤

፭/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ቁጥጥር የሚካሄድበትን የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤

፮/ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ተቆጣጣሪው ሥልጣኑን አለአግባብ በመጠቀም ለሚፈፅመው ድርጊት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፤

፯/ ማንኛውም ኤጀንሲ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ተቆጣጣሪው ተግባሩን በሚያከናውንበት ጊዜ የመተባበር ግዴታ አለበት፤

e) enter the office of any agency, at any time during working hours, and examine necessary documents, records, books of accounts and other similar documents, and make inquiries thereof.

3/ The overseas employment inspector, while conducting inspection pursuant to Sub-Article (2) of this Article, shall keep with and show his identity card issued to him by the Ministry or the appropriate authority;

4/ The overseas employment inspector shall submit, the findings of the inspection conducted pursuant to Sub-Article (3) of this Article to the Ministry or the appropriate authority together with his recommendations on legal measures to be taken;

5/ The Ministry may issue directive on the procedures of conducting inspections pursuant to Sub-Article (3) of this Article;

6/ The overseas employment inspectorate shall be held accountable for abuse of power in accordance with appropriate law;

7/ Any Agency shall have obligation to cooperate for the proper implementation of the responsibility of overseas employment inspector;

https://ethiodata.et/

፰/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለስልጣን በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ ፰ እስከ አንቀጽ ፲ የተገለጹት ተቋማት በዚህ አዋጅ የተጣለባቸውን ግዴታና ኃላፊነት እየተወጡ ስለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

## ክፍል አራት

## በኤጀንሲ ስለሚሰጥ የሥራ ስምሪት አገልግሎት እና ስለኤጀንሲዎች ደረጃ

### ንዑስ ክፍል አንድ

### ስለፈቃድ፣ ለፈቃድ ብቁ ስለመሆንና ስላለመሆን

**፴ . ስለፈቃድ**

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት ኤጀንሲ ሆኖ ለመሥራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

፪/ ከባህረኛ ላኪ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰውን ፈቃድ ለማግኘት ሚኒስቴሩ ካወጣቸው ከአንድ እስከ አምስት ደረጃዎች አንዱን መምረጥ እና ለተመረጠው ደረጃ በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ፈቃድ በማውጣት ከአንድ ሀገር በላይ ለመሥራት የሚፈልግ ሰው ለእያንዳንዱ ሀገር ፈቃድ ማውጣት ያለበት ሲሆን ይህም ቀድሞ በተሰጠው ፈቃድ ላይ የሚገለጽ ይሆናል፡፡

፬/ ኤጀንሲዎች የሚያወጡት ፈቃድ በሚኒስቴሩ የሥራ ገበያ መረጃ ስርአት በኩል ይከናወናል።

፭/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፬) ለተዘረዘሩት ሚኒስቴሩ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

8/ The Ministry or the appropriate authority shall follow up and supervise institutions that are given powers and duties pursuant to provisions of Article 8 to Article 10 of this Proclamation, to ensure they are duly discharging the powers and duties vested in them.

## PART FOUR

## OVERSEAS EMPLOYMENT SERVICE THROUGH AN AGENCY AND AGENCY RANKING

### SUB-SECTION ONE

### LICENSE, ELIGIBILITY AND NON-ELIGIBILITY FOR LICENSE

**30.License**

1/As per this proclamation, any person wishing to operate as an Agency shall obtain a license from the Ministry.

2/ Except for deploying seafarers, to obtain the license mentioned in Sub-Article (1) of this Article, one must select one of the five levels issued by the Ministry and fulfill the requirements set forth in this Proclamation for the chosen level.

3/Any person who desires to obtain the license as per Sub-Article (1) above and function in more than one country shall obtain separate license for each country of operation and this fact shall be indicated on the licenses already taken.

4/ Agency licenses shall be processed through the labor market information system of the Ministry.

5/ The Ministry shall issue Directive for provisions stated from Sub Article (1) up to Sub Article (4) of this Article.

https://ethiodata.et/

## ፴፩. ፈቃድ ለማግኘት ብቁ ስለመሆን

፩/ በዚህ አዋጅና በሌሎች ሕጎች መሠረት በውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ዘርፍ እንዳይሰማራ ያልተከለከለ፣መሆን ይኖርበታል፤

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፮ ላይ ስለ ዋስትና ከተደነገገው በተጨማሪ አመልካቹ ግለሰብ ሆኖ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው እና ፈቃድ ለጠየቀበት ደረጃ የሚጠበቅበትን የካፒታል መጠን ያሟላ፤

ሀ) ለደረጃ አንድ ፳ ሚሊዮን ብር (፳ ሚሊዮን) ካፒታል ወይም አክሲዮን ወይም መዋጮ ያለው፤

ለ) ለደረጃ ሁለት ፲፭ ሚሊዮን ብር (አስራ አምስት ሚሊዮን ብር) ካፒታል፣ አክሲዮን ወይም መዋጮ ያለው፤

ሐ) ለደረጃ ሶስት ፲ ሚሊዮን ብር ( አስር ሚሊዮን ብር ) ካፒታል ፣ አክሲዮን ወይም መዋጮ ያለው፤

መ) ለደረጃ አራት ፯ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር ( ሰባት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ ብር) ካፒታል ፣ አክሲዮን ወይም መዋጮ ያለው፤

ሠ) ለደረጃ አምስት ፭ ሚሊዮን ብር (አምስት ሚሊዮን ብር ) ካፒታል ፣ አክሲዮን ወይም መዋጮ ያለው፤

፫/በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፮ ላይ ስለ ዋስትና ከተደነገገው በተጨማሪ አመልካቹ የንግድ ማኅበር ከሆነ የተቋቋመበት ዓላማ በውጭ ሀገር ሥራና ሠራተኛ የማገናኘት አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋመ፣ የንግድ ማህበሩ አባላት በሙሉ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያላቸው እና በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተቀመጠው የተዋጣ አክሲዮን ወይም መዋጮ ያለው፣

## 31. Eligibility for Obtaining License

1/ The applicant shall not be a person prohibited to operate in overseas employment service pursuant to this Proclamation or other relevant laws;

2/ Without prejudice to guarantee provisions stipulated in Article 66 of this Provision and other laws, an applicant who is an Ethiopian and a sole proprietor must meet the capital requirements that corresponds to the chosen level;

a) For Level one, 20 Million Birr (Twenty Million Birr ) in capital, shares, or contribution;

b) For Level two, 15 million Birr (Fifteen Million Birr ) capital, shares, or contribution;

c) For Level three, 10 Million Birr (Ten Million Birr ) capital, shares, or contribution;

d) For Level four, 7.5 million Birr (Seven Million Five Hundred Thousand Birr) capital, shares, or contribution;

e) For Level five, 5 million Birr (Five Million Birr) capital, shares, or contribution is required;

3/ In addition to what has been proclaimed about guarantee on Article 66, if the applicant is a company which is established to engage in overseas employment service, all the members shall be Ethiopian citizens and have a paid-up capital or contribution specified in Sub-Article (2) of this Article;

https://ethiodata.et/

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገው ቢኖርም የሰለጠነ የሰው ኃይል በውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ላይ እንዲሰማራ ለማድረግ ከኢትዮጵያዊ ጋር ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወይም የውጭ ሀገር ዜጋ በኤጀንሲነት ተቋቁመው መሥራት የሚችሉት፡-

ሀ) አመልካቹ በሽርክና ማኅበር ወይም ኃላፊነቱ በተወሰነ የግል ማኅበር ወይም በአክስዮን ማኅበር የተቋቋመ ድርጅት ከሆነ ለተጠየቀው ደረጃ የአክሲዮን ድርሻ ሰባ አምስት በመቶ (፸፭) በመቶ ከኢትዮጵያውያዊ ሃያ አምስት (፳፭) በመቶ ትውልደ ኢትዮጵያዊ ሆኖ በድምሩ በንዑስ አንቀጽ (፪) ከተቀመጠው ያላነሰ የተዋጣ መዋጮ ያለው፤

ለ) አመልካቹ በሽርክና ማኅበር ወይም ኃላፊነቱ በተወሰነ የግል ማኅበር ወይም በአክስዮን ማኅበር የተቋቋመ ድርጅት ከሆነ የአክሲዮን ድርሻ ሰማንያ (፹) በመቶ ኢትዮጵያዊ፤ ሃያ (፳) በመቶ የውጭ ሀገር ዜጋ ሆኖ በድምሩ በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፪) ያላነሰ የተዋጣ መዋጮ ያለው መሆን አለበት፤

፭/ ከፍተኛ የዘርፍ ዕውቀት እንዲሁም ዓለምአቀፍ ልምድ እና የሥራ ትስስር የሚጠይቁ ባህረኞች እና ሌሎች ተመሳሳይ ሙያተኞችን ከሥራ ጋር የማገናኘት አገልግሎትን በተመለከተ የውጭ ሀገር ዜጎች ሙሉ የአክሲዮን ድርሻ ይዘው ኤጀንሲ እንዲያቋቁሙ ሚኒስቴሩ ሊፈቅድ ይችላል።

4/ Notwithstanding the provisions of Sub-Articles (1) and (2) of this Article, in order to have skilled workers deployed in overseas employment, a foreign national of Ethiopian origin, or a foreign national may jointly establish and operate an agency with an Ethiopian in overseas employment of skilled labor under the following conditions:

a) If the applicant is partnership or Share Company or Private Limited Company (PLC) and the members of the company with a share of 75% (Seventy-Five per cent) from Ethiopian nationals, 25% (Twenty-Five per cent) from foreign nationals of Ethiopian origin whose paid-up contribution is no less than that specified in Sub-Article (2) of this article for the requested level;

b) If the applicant is partnership or Share Company or Private Limited Company (PLC), it shall have 80% (Eighty per cent) of its share capital from Ethiopian nationals and 20% (Twenty per cent) from foreign nationals whose paid-up contribution is no less than that specified in Sub-Article (2) of this Article;

5/ For overseas employment services targeting seafarers and other similar sectors that require high sectoral knowledge, international experience and professional networks, the Ministry may allow foreign nationals to establish agencies with full share ownership.

https://ethiodata.et/

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለተጠየቀው ደረጃ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፮ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው የዋስትና ገንዘብ በአክሲዮን ድርሻቸው መጠን ኢትዮጵያዊ እና ትውልደ ኢትዮጵያዊ በብር፣ የውጭ ሀገር ዜጋ ደግሞ በውጭ ምንዛሬ የሚያስቀምጡ ይሆናል፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተጠቀሱትን መነሻ ካፒታል መጠን የባንክ ወይም የአክሲዮን ማረጋገጫ መቅረብ ይኖርበታል።

**፴፪. ፈቃድ ለማግኘት ብቁ የማያደርጉ ሁኔታዎች**

ከዚህ በታች የተመለከቱት ፈቃድ ለማግኘት ብቁ አይሆኑም፦

፩/ አዋጅ ቁጥር ፱፻፳፫/፪ሺ፰ እና አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፵፮/፪ሺ፲፫ ፣ በዚህ አዋጅ ወይም አዋጁን ለማስፈጸም የወጣ ደንብ ወይም መመሪያ በመጣስ፦

ሀ) ፈቃዱ የተሰረዘበት ወይም ለሦስት ጊዜ እና ከዚያ በላይ ፈቃዱ የታገደበት ማንኛውም ኤጀንሲ፣ አባሎቹ እና ኤጀንሲው የአክሲዮን ማኅበር ከሆነ የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት፤

ለ) የሠራተኞች መብት፣ ደህንነት እና ክብር በመጣሱ ምክንያት ለቀረቡ አቤቱታዎች መፍትሔ ባለመስጠቱ ፈቃዱ የተሰረዘበት፤

6/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (4) paragraph (a) and (b) of this Article, the guarantee amount specified in Article 66 (1) of this Proclamation for the requested level shall be deposited by Ethiopian and foreign nationals of Ethiopian origin in Birr and foreign nationals in foreign currency, in proportion to their shareholding.

7/ A bank or share certificate confirming the initial capital amount mentioned in Sub-Article (2) of this Article shall be submitted.

**32. Non-eligibility to Obtain License**

The following shall not be eligible to obtain license:

1/ In contravention of Proclamation No. 923/2016, Proclamation No. 1246/2021, this Proclamation and Regulations or Directive issued there-under:

a) any Agency, its members or in cases where the Agency is a share company, the Board of Directors whose license had been revoked or suspended more than three times;

b) any agency or its members whose license had been revoked for failure to provide remedies for complaint against it for violations of the rights, safety and dignity of workers;

https://ethiodata.et/

፪/ በሰው መነገድና ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር፣ በተደራጁ ወንጀሎች፣ በሽብርተኝነት፣ በአደንዛዥ ዕፅ ዝውውር ወይም በሕገወጥ የገንዘብ ዝውውር ወንጀል፣ በማጭበርበር፣ በሙስና፣ በወንጀል የተገኘ ንብረት ሕጋዊ ማስመሰል፣ ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት፣ ሕገ-ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር እና የመሳሰሉ ወንጀሎች ጋር በተያያዘ ተከሶ በፍርድ ቤት የተቀጣ ሰው ወይም ከላይ በበተዘረዘሩት ወንጀሎች ተከሶ ጉዳዩ በፍርድ ቤት በመታየት ላይ ያለ ሰው፤

፫/ የጉዞ ወኪል ወይም የአየር መንገድ ትኬት ሽያጭ ቢሮ ወይም የወኪሉ ወይም የቢሮው ሠራተኛ ትራንዚተር፤

፬/ የሚኒስቴሩ፣ አግባብ ያለው ባለሥልጣን፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት የፖሊስ ኮሚሽን ወይም ይህን አዋጅ በቀጥታ የሚያስፈጽም የመንግሥት አገልግሎት ሠራተኛ ማንኛውም የሥራ ኃላፊ፣ ሠራተኛ ወይም በውጭ ሀገር የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ አመራር አባል እና የእነዚሁ ቤተሰቦች፡፡

፴፫. **ስለ ኤጀንሲዎች ደረጃ**

ሚኒስቴሩ ኤጀንሲዎች በሚያሰማሩት የሰው ኃይል ብዛት፣ ክህሎት፣ እና የሙያ ዘርፍ፣ መነሻ ካፒታል እንዲሁም ተያያዥ መስፈርቶችን ታሳቢ በማድረግ ከአንደኛ እስከ አምስተኛ ደረጃ የያዘ ፈቃድ ለኤጀንሲዎች ይሰጣል።

2/ An individual accused and sentenced by the court of law for his engagement in human trafficking, smuggling of migrants, organized crime, terrorism activity, transfer of narcotic substances or money laundering or individual charged for the crime and whose case is pending before a court of law until decision is rendered;

3/ Travel agency, ticket office of airlines or employee of the travel agency or transistor;

4/ Any official or employee in the Ministry, the appropriate authority, Ministry of Foreign Affairs, Main Department for Immigration and Citizenship, Police Commission or any governmental organ entrusted to implement this Proclamation or Ethiopian community overseas in leadership position or the families of these individuals.

**33. Levels of Agencies**

The Ministry shall issue licenses to agencies, ranging from Level One to Level Five, on the basis of the number of workers they deploy, skill sets of workers, professional mix, startup capital of the agencies, and other related criteria.

https://ethiodata.et/

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## ስለፈቃድ አሰጣጥ

### ፴፬. ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ስላለባቸው መሥፈርቶች

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፩ መሠረት ብቁ የሆነ ማንኛውም አመልካች ፈቃድ ለማግኘት ለዚሁ አላማ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር አሟልቶ በሥራ ገበያ መረጃ ስርዓት ቋት ላይ መመዝገብ ይኖርባቸዋል፦

፩/ በኤጀንሲነት ሥራ ለመሰማራት የሚያስችለው የንግድ ምዝገባ እና የንግድ ስያሜ የምስክር ወረቀት የያዘ የንግድ ፈቃድ፤

፪/ አመልካቹ ሥራውን የሚያካሂደው በንግድ ማኅበርነት ከሆነ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ አገልግሎት የተረጋገጠ የመመሥረቻ ጽሁፍ፤

፫/ አመልካች ፈቃድ ለማውጣት የጠየቀው በግል ከሆነ ግለሰቡ፣ በሽርክና ማኅበርነት ከሆነ የማህበሩ አባላት ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ወይም በአክሲዮን ማኅበር ከሆነ የዳይሬክተሮች ቦርድ እና አመራር አካላት እንዲሁም የሥራ ኃላፊዎችና ተቀጣሪ ሠራተኞች ከወንጀል ነፃ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ከፖሊስ የተሰጠ ማስረጃ እና የባዮሚትሪክስ መረጃዎች፤

፬/ የአደረጃጀት መዋቅሩን የሚያሳይ ቻርት፣ ለሥራ የሚያስፈልግ የሰው ኃይል ዝርዝርና የትምህርት ማስረጃ፣ የእያንዳንዱ ኃላፊና ሠራተኛ የሥራ መደብ፣ የግል ታሪክ፤

## SUB-SECTION TWO

## ISSUANCE OF LICENSE

### 34. Requirements to Obtain License

Any applicant who is eligible to obtain a license pursuant to Article 31 of this Proclamation shall fill in the application form prepared for such purpose, and shall register and submit, in the labor market information system, the form along with a complete list of the following documents:

1/ Certificate of Business Registration and Trade Name enabling the applicant to operate as an Agency;

2/ Where the applicant operates the activity as a business association, copies of its Memorandum of Association authenticated by the Documents Authentication and Registration Services;

3/ If the applicant is an individual applying for a license, then the individual; if it is a partnership, the members of the partnership; or if it is a private limited company or a share company, the board of directors and management, as well as the supervisors and employed staff, must all provide criminal record clearance from the police, along with their biometrics data;

4/ A chart showing the organizational structure of the Agency; list of required human resources together with educational qualifications; job position and employment personal history of each officer and employee;

https://ethiodata.et/

፭/ የአመልካቹ የሥራ ቦታ አድራሻና የቢሮው ይዞታ የራስ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ወይም ኪራይ ከሆነ የኪራይ ውል በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ አገልግሎት የተረጋገጠ ዋና ቅጂ፤

፮/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፮ (፩) የተመለከተውን የዋስትና ግዴታ ማሟላቱን የሚገልፅ ማረጋገጫ ሰነድ፤

፯/ የኤጀንሲው ሥራ አስኪያጅ እና የሌሎች ሠራተኞችን የትምህርት ማስረጃ ቅጂዎች፣

፰/ ሥራ አስኪያጁ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ እና በሥራ አመራር ሦስት ዓመት የሥራ ልምድ ያለው ስለመሆኑ ማረጋገጫ ሰነድ፤

፱/ ሥራው የሚቋቋመው በግለሰብ ከሆነ ባለቤቱ እና ሥራ አስኪያጁ፣ በንግድ ማኅበርነት ከሆነ የማኅበሩ አባላትና የአመራር አካላት በቅድመ ፈቃድ ሥልጠና ላይ ስለመሳተፋቸው የሚገልፅ የምስክር ወረቀት፤

፲/ ሠራተኛን በሚልክበት ሀገር፦

ሀ) የተሟላ ቢሮ ስለመክፈቱ ወይም የተቀባይ ሀገር ዜግነት ያለውና በሀገሩ አግባብ ባለው የመንግሥት አካል በሥራና ሠራተኛ አገናኝነት ሥራ ላይ ለመሳተፍ የሚያስችል ፈቃድ ያለውን ሰው በውክልና ስለመሰየሙ የተረጋገጠ ማስረጃ፤

5/ Office address of the applicant, and certificate of ownership if he is the owner of the office or the original copy of the contract of lease authenticated by the Documents Registration and Authentication Services if the office is leased one;

6/ Verification document to the effect that the security bond pursuant to Article 66 (1) of this Proclamation is complied with;

7/ Copy of educational credentials of the General Manager and other employees of the Agency:

8/ A document confirming that the General Manager has at least first degree and three years of work experience on managerial position;

9/ Certificate testifying the pre-license training attendance of the owner and the General Manager if the activity is operated by sole proprietor; or the members and management bodies if it is operated by a business organization;

10/ In the country of destination:

a) Verification document showing that the applicant has opened a full-fledged office in the receiving country or has representative who is a citizen of the receiving country who is duly licensed to engage in overseas employment services;

https://ethiodata.et/

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተመለከተው ተወካይም ውክልናውን ስለመቀበሉ በሚመለከተው ሚሲዮን ወይም በተቀባዩ ሀገር ሚሲዮን ከሌለ አዲስ አበባ በሚገኘው የተቀባዩ ሀገር ሚሲዮን ወይም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ ሰነድ ማስረጃ፤ እና

ሐ) ለሠራተኛው ጊዜያዊ የምግብና የመጠለያ አገልግሎት መስጫ ቦታ ያዘጋጀ ስለመሆኑ በሚመለከተው ሚሲዮንና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ ደብዳቤ፤

መ) የኮሚሽን ክፍያ የስምምነት ሰነድ፤

፲፩/ ቀደም ሲል ፈቃድ ተሰጥቶት ሲሰራ በነበረበት ጊዜ የሚፈለግበትን ግብር የከፈለ ስለመሆኑ ማስረጃ፤

፲፪/ የፈቃድ ክፍያ መፈጸሙን ማረጋገጫ፤

**፴፭. <u>ፈቃድ ስለመስጠት</u>**

ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ ለማግኘት የሚያበቁ ሁኔታዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ ለአመልካቹ እንደየደረጃው ዓይነት ፈቃድ ይሰጣል፤ የቀረበው የፈቃድ ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ከሆነም በ፯ የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ለአመልካቹ ያሳውቃል፡፡

**፴፮. <u>ፈቃድ ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ</u>**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፭ መሠረት የተሰጠ ፈቃድ ለአንድ ዓመት የፀና ይሆናል፡፡

b) A verification document showing that the representative pursuant to paragraph (a) of this Sub-Article has accepted the delegation, and the verification shall be made by the concerned Mission, or if there is no Ethiopian Mission in the country of destination through the latter's mission in Addis Ababa which must also be confirmed by the Ministry of Foreign Affairs; and

c) That the applicant has a facility for providing temporary services of food and sheltering to the workers and produce a letter to this confirmed by the concerned Mission and the Ministry of Foreign Affairs;

d) The contract document showing the commission fee;

11/ Tax clearance certificate that the applicant has paid all taxes due during his prior licensed operation;

12/ Confirmation showing payment of license fee;

**35. <u>Issuance of License</u>**

Whenever the Ministry ensures that the requirements for issuing license as per this Proclamation are met, it shall issue the license to the applicant; if the application for license is not acceptable, such denial shall be notified to the applicant within 7 working days.

**36. <u>Validity Period of License</u>**

A license pursuant to Article 35 of this Proclamation shall remain valid for one year.

https://ethiodata.et/

**፴፯. ፈቃድን በግልፅ ቦታ ስለማስቀመጥ**

ማንኛውም ኤጀንሲ በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠውን ፈቃድ በከፈተው ቢሮ ውስጥ ግልፅ ሆኖ በሚታይ ቦታ ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡

**፴፰. የሥራ ፈቃድ ማስተላለፍ እና ከአንድ ኤጀንሲ በላይ መሳተፍ የተከለከለ ስለመሆኑ**

፩/ ማንኛውም ኤጀንሲ በሚኒስቴሩ የተሰጠውን ፈቃድ ለሌላ ሰው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ማስተላለፍ ክልክል ነው፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው ከአንድ ኤጀንሲ በላይ ባለቤት፣ የሽርክና ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር አባል፣ የቦርድ አመራር፣ ሥራ አስኪያጅ ወይም ሠራተኛ ሆኖ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ መሥራት አይችልም፡፡

፫/ ማንኛውም ኤጀንሲ በሌሎች ሕጎች የሽርክና ማህበራት አባላትን መጨመርም ሆነ መቀነስ የሚችሉ ስለመሆኑ ቢደነግግም ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም በሽርክና ወይም ኋላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ላይ አዲስ አባል ሲጨምርም ሆነ ነባር አባልን ሲቀንስ ለሚኒስቴሩ ሳያሳውቅ መተግበር አይችልም።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ቢኖርም ኤጀንሲው በግለሰብ የተቋቋመ ከሆነና ግለሰቡ ከሞተ ለሥራ ወደ ውጭ ሀገር የተላኩ ዜጎች መብት፣ ደህንነትና ክብር ለማስጠበቅ ሲባል ብቻ ሥራውን ላለማስተጓጎልና ለማጠናቀቅ በግለሰቡ በፍርድ ቤት ሕጋዊ ወራሽነታቸው ለተረጋገጠ ወራሾች በጠየቁ ግዜ የሥራ ፈቃዱ ለነዚህ ወራሾች ሊተላለፍ ይችላል፡፡

**37. Display of License in Conspicuous Place**

Any Agency shall display the license issued to it in accordance with this Proclamation in its office in a conspicuous place.

**38. Non-transferability of License and Prohibition of Engagement in more than one Agency**

1/ Any Agency shall in no way, directly or indirectly, transfer the license issued to him by the Ministry to any other person.

2/ Any person cannot operate in more than one Agency, directly or indirectly, as owner, a member of partnership or Private Limited Company, Board of directors, General manager or an employee.

3/ Notwithstanding provisions in other laws permitting agencies to increase or decrease partners in a partnership or members in a private limited company, no agency shall add or remove a partner or a member without prior notification to the Ministry for the purpose of implementing this Proclamation.

4/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, where the Agency is established as sole proprietor and in case of death of the sole proprietor, the license may devolve to judicially ascertained heirs, upon their request, for the sole purpose of protecting the rights, safety and dignity of workers by preventing disruption of operation in the Agency and until winding up of its operation.

https://ethiodata.et/

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተመለከቱት ወራሾች በዘላቂነት ሥራውን ማስቀጠል ከፈለጉ ሚኒስቴሩ ጠያቂዎቹ ለፈቃድ ብቁ መሆናቸውን በማረጋገጥ ፈቃዱን ሊያስተላልፍላቸው ይችላል፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) እና (፭) መሰረት ሕጋዊ ወራሾች የኤጀንሲውን ሥራ ካላስቀጠሉ፤

ሀ) በተላኩ ዜጎች ላይ የደረሰ ጉዳት ካለ በኢንሹራንስ እና በዋስትና የተያዘው ተቀማጭ ገንዘብ የማይሸፈን ኋላፊነት ካለ ከውርሱ የሚሸፈን ይሆናል።

ለ) በኤጀንሲው በተላኩ ዜጎች ላይ ወደ ፊት ሊደርስ የሚችል ጉዳት ካለ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚኖርበት ከገንዘብ ጋር የተያያዘ ኋላፊነት ለሕጋዊ ወራሾቹ ከውርሱ ባገኙት መጠን የሚተላለፍ ይሆናል።

**፴፱. <u>የአመራር ወይም የሠራተኛ ለውጥ ስለማሳወቅ</u>**

ማንኛውም ኤጀንሲ የቦርድ አመራር ወይም የሥራ አስኪያጅ ለውጥ ሲያደርግ ወይም ሠራተኛን ሲቀጥር ወይም ሲያሰናብት ይህንኑ እንደአግባቡ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለሥልጣን ወዲያውኑ በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

**፵. <u>የቢሮ አድራሻ ለውጥ ስለማድረግና ስለማሳወቅ</u>**

ማንኛውም ኤጀንሲ፦

፩/ የቢሮ አድራሻ ለውጥ ማድረግ የሚችለው ቢሮው የተሟላ እና ባለሙያዎች መኖራቸውን እንደአግባቡ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን አረጋግጦ ሲፈቅድለት ብቻ ነው፤

5/ Where the heirs specified under Sub-Article (4) of this Article seek to resume the operation of the Agency, the Ministry may transfer the license to them upon ascertaining that they meet the requirements for obtaining a license.

6/ Where the legal heirs do not resume the operation of the Agency as per Sub-Articles (4) and (5) of this Article;

a) Any damage to overseas workers, if any, not covered by insurance and security deposit fund shall be covered from the inheritance;

b) Any future damage likely to occur to overseas workers, any monetary liability that may ensue to the Agency in accordance with this proclamation shall pass to the heirs in proportion to their share that devolves from the inheritance.

**39.<u>Notification of Change of Management or an Employee</u>**

Any Agency shall, upon making change to its Board of Director or General Manager or recruit or dismiss any employee, immediately notify same in writing to the Ministry or the appropriate authority.

**40. <u>Change of Office Address and Notification</u>**

Any Agency:

1/ May change its office address only after the Ministry or the appropriate authority verifies and approves that the office complies with the requirements;

https://ethiodata.et/

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በኤጀንሲው የቀረበውን የቢሮ አድራሻ ለውጥ ጥያቄ ሚኒስቴሩ ካልተቀበለው ምክንያቱን ገልፆ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፤

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ተፈቅዶ የተፈፀመውን የቢሮ አድራሻ ለውጥ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ ሰፊ ሽፋን እና ሕጋዊ ሰውነት ባላቸው የመገናኛ ብዙኃን ላይ ለሕዝብ በማሳወቅ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለሥልጣን ማስረጃውን ማቅረብ አለበት፡፡

## ፵፩. ስለ ፈቃድ ዕድሳት

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጥ ፈቃድ በየዓመቱ የሚታደስ ይሆናል፡፡

፪/ ማንኛውም ኤጀንሲ ፈቃድ ለማደስ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው የጊዜ ገደብ ከማለቁ በፊት ባለው አንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለዚሁ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት የሚከተሉትን ሰነዶች አሟልቶ በሥራ ገበያ መረጃ ስርዓት በኩል ለሚኒስቴሩ ማቅረብ ይኖርበታል፦

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፮ (፩) የተመለከተውን የዋስትና ግዴታ ባለው የእለቱ የምንዛሬ ዋጋ ልክ ተቀማጭ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ፤

ለ) ግብር የተከፈለ ስለ መሆኑ ማስረጃ፤

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፬ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተዘረዘሩት አካላት ከወንጀል ነፃ ለመሆናቸው ከፖሊስ ማስረጃ፤

2/ Where the Ministry disapproves the request of the Agency for change of office pursuant to Sub-Article (1) of this Article, it shall notify to the Agency with the reasons thereof within seven working days;

3/ Shall notify the change of office address effected up on approval pursuant to Sub-Article (1) of this Article, within seven working days, on one of the legally recognized mass media outlets to the public and submit evidence of same to the Ministry or the appropriate authority.

## 41. Renewal of License

1/A license issued in accordance with this Proclamation shall be renewed every year.

2/ In order to renew a license, any Agency shall, one month prior to the expiry of the period specified under Sub-Article (1) of this Article, fill an application form and submit it together with the following documents to the Ministry through labor market information system:

a) evidence of the deposit of a guarantee obligation, pursuant to Article 66 (1) of this Proclamation, the amount of which shall be based on exchange rate of the date;

b) evidence of payment of tax;

c) criminal record clearance from Police as specified in Sub-Article (3) under Article 34 of this Proclamation;

https://ethiodata.et/

መ/ በተቀባይ ሀገር የተሰየመው ወኪል የታደሰ የንግድ ፈቃድ ማስረጃዎች፤

ሠ) ለሥራ ወደ ውጭ ሀገር ስላሰማራቸውና ስለተመለሱት ሠራተኞች የሚገልፅ አጠቃላይ ሪፖርት፤

ረ) ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የተወሰኑ ሌሎች ማስረጃዎች፡፡

፫/ ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ ለማደስ የሚያበቁ ሁኔታዎች መሟላታቸውን እንዳረጋገጠ የፈቃድ ዕድሳት ክፍያ እንዲፈጽም በማድረግ በሶስት የሥራ ቀን ውስጥ ፈቃድ ያድሳል፤ የቀረበው የፈቃድ ዕድሳት ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ከሆነም በዚሁ ጊዜ ውስጥ ለአመልካቹ በጽሁፍ ያስታውቃል፡፡

፬/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፮ መሠረት ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ሲጠናቀቅ ያልታደሰ የኤጀንሲ ፈቃድ ታግዶ ይቆያል፡፡

፭/ ኤጀንሲው ፈቃዱን በወቅቱ ሳያሳድስ የቀረ እንደሆነ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ካበቃበት በ፩ወር ውስጥ የሚታደስ ሆኖ ይህ ጊዜ ካለፈ በኋላ ባለ ፩ወር ግዜ ውስጥ ደግሞ ፩፻ሺ ብር(አንድ መቶ ሺ ብር) ከፍሎ የሚያሳድስ ይሆናል፣ ይህ ቀን ካለፈ ፈቃዱ ይሰረዛል።

d) evidence of renewed license of its representative in the receiving country;

e) general report that indicates the status of deployed and returned overseas workers;

f) other evidence specified in the Directives of the Ministry.

3/ After ascertaining that the Agency has met the requirements for license renewal, the Ministry shall, up on causing to pay license renewal fee, issue the renewed license within three working days; where the application for license renewal is denied, such denial shall be notified in written to the applicant within the same timeline.

4/ The license not renewed within the validity period specified under Article 36 of this Proclamation shall remain suspended.

5/ Where an Agency fails to renew its license in due time, its license may be renewed within one month following the expiry date; and if this timeline also expires, the license shall be renewed within the next one month upon payment of Birr 100,000.00 (One Hundred Thousand Birr), and afterwards the license shall be revoked.

https://ethiodata.et/

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) እና (፭) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ኤጀንሲው ፈቃዱን ያላሳደሰው አግባብነት ባለው ሕግ መሰረት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑ በማስረጃ ሲረጋገጥ እና በተቋሙ የበላይ ኃላፊ ሲወሰን ፍቃዱ የሚታደስለት ይሆናል።

፯/ ኤጀንሲው ፈቃዱን ሳያሳድስ የቆየው በአስተዳደራዊ የእግድ ቅጣት ታግዶ የቆየ ከሆነ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተቀመጠው የግዜ ገደብ ተፈጻሚ ይሆናል።

**፵፪. ፈቃድ አውጥቶ ሠራተኛ አለመላክ**

፩/ አንድ ኤጀንሲ ፈቃድ አውጥቶ በስድስት ወር ግዜ ውስጥ አንድም ሠራተኛ ወደ ሥራ ካላሰማራ ሚኒስቴሩ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በሰጠ በሰላሳ የሥራ ቀናት ውስጥ ቢያንስ ሃያ አምስት ሠራተኛ ያላሰማራ ኤጀንሲ ወዲያውኑ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ፈቃድ ያወጣ ማንኛውም ኤጀንሲ ፍቃዱ ጸንቶ ባለበት የግዜ ገደብ ውስጥ ቢያንስ ሃምሳ ሰው ካልላከ ፈቃዱ ይሰረዛል።

፬/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገው ቢኖርም ኤጀንሲው ሠራተኛ ማሰማራት ያልቻለው ሚኒስቴሩ ሠራተኛ ሳይመደብለት የቀረ ከሆነ እና ኤጀንሲው ሕጋዊ የጽሑፍ ማስረጃ ማቅረብ ከቻለ ከዚህ በላይ የተደነገጉት ንዑስ አንቀጾች ተፈጻሚ አይሆኑም።

6/ Without prejudice to Sub-Article (4) and (5) of this Article, where the failure of the Agency to renew its license is proved to be due to force majeure in accordance with the appropriate law and upon the decision of the head of the institution, the license may be renewed.

7/ The timeline provided in Sub-Article (3) of this Article shall be applicable where the Agency's failure to renew the license is due to suspension as an administrative measure.

**42. Failure to Deploy Workers after Obtaining License**

1/ The Ministry shall issue a written warning to an Agency that does not deploy any overseas worker within six months after obtaining license.

2/ Any Agency that failed to deploy at least 25 workers within 30 working days after the warning shall have its license revoked.

3/ Without prejudice to Sub-Article (2) of this Article, any licensed Agency which failed to deploy at least 50 overseas workers issued with a license shall have its license revoked.

4/ Notwithstanding the provisions from Sub-Articles (1) up to (3) of this Article, if the agency is not able to deploy workers because the Ministry does not assign workers, and the agency can provide legal written evidence, then the above provisions shall not apply.

https://ethiodata.et/

**፵፫. ለኤጀንሲዎች ስለሚሰጥ እውቅና እና ማበረታቻ**

፩/ ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፫ የተጠቀሱትን ደረጃዎች መሰረት ያደረገ እውቅና እና ማበረታቻ ለኤጀንሲዎች ይሰጣል።

፪/ ሚኒስቴሩ የመዳረሻ ሀገራት ብዛትን፣ የሚሰማራ የሰው ኃይል ክህሎት እና መሰል መስፈርቶችን መሰረት ያደረገ እውቅና እና ማበረታቻ ይሰጣል፤አፈፃፀሙን በተመለከተ ሚኒስቴሩ መመሪያ ያወጣል።

**43. Recognition and Incentive Scheme for Agencies**

1/ The Ministry shall grant recognition and incentives pursuant to the ranks specified in Article 33 of this Proclamation.

2/ The Ministry shall grant recognition and incentives based on the country of destination, the skills of deployed workers, and similar criteria. The Ministry shall issue a detailed implementation directive for this purpose.

## ንዑስ ክፍል ሦስት

## ስለ ሥራ ስምሪት አገልግሎት

## SUB-SECTION THREE

## EMPLOYMENT SERVICE

**፵፬. ስለ ሠራተኛ ምልመላ**

፩/ ማንኛውም ወደ ውጭ ሀገር ሥራ መሰማራት የሚፈልግ ዜጋ ምልመላ የሚከናወነው ከአንድ ማዕከል አገልግሎት ጀምሮ በተዘረጋው የኢትዮጵያ የሥራ ገበያ መረጃ ሥርዓት በኩል ብቻ መሆን አለበት፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ የሠራተኞችን ምልመላና ስምሪት በሥራ ገበያ መረጃ ስርዓት በኩል መሆኑን ይከታተላል፣ ይደግፋል አፈጻጸሙንም ይቆጣጠራል፡፡

**44. Recruitment of Worker**

1/ Recruitment of any worker desiring to be deployed in overseas employment shall be conducted through the centralized labor market information system only.

2/ The Ministry shall follow up, support and control that the recruitment and deployment of workers is conducted through labor market information system.

https://ethiodata.et/

**፵፭. የሥራ ውልን ስለማፅደቅ**

፩/ መንግስት ለመንግስት፣ በኤጀንሲና በግል ጥረት ለሚደረግ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፯ መሰረት በተዘጋጀው ሞዴል የሥራ ውል ተዘጋጅቶ በአሠሪ፣ ሠራተኛና እንደ ሁኔታው በኤጀንሲ ተፈርሞ በሥራ ገበያ መረጃ ስርአት ወይም እንደአግባቡ በሚኒስቴሩ መጽደቅ ይኖርበታል፡፡

፪/ አሠሪ ወይም ኤጀንሲ የሥራ ውልን ለማጸደቅ በሕግ የተቀመጠውን መስፈርት በማሟላት አግባብ ላለው ባለስልጣን በማቅረብ ተመርምሮ ሲረጋገጥ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

**፵፮. ሠራተኛን ለሥራ ስለማሰማራትና ስለማሳወቅ**

፩/ ማንኛውም ኤጀንሲ፦

ሀ) የሥራ ውል በፀደቀ በተከታታይ የ፲፭ ቀን ጊዜ ውስጥ ሠራተኛን ለሥራ ማሰማራት አለበት፤

ለ) ወደ ውጭ ሀገር ለሥራ የላከውን ሠራተኛ በሚሄድበት ሀገር የመኖሪያ ፈቃድ ወይም በመዳረሻ ሀገር ለመኖር የሚያስችል ህጋዊ ሰነድ እና የሥራ ፈቃድ ለማግኘቱ የማረጋገጥና ይህንኑ መረጃ አሟልቶ በተከታታይ ፴ ቀናት ውስጥ ሆኖ ለሚኒስቴሩ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

**45. Approval of Contract of Employment**

1/ Overseas deployment of workers through government to government correspondence or Agency and personal effort shall be reduced into a contract which shall be in accordance with the model contract prepared by the Ministry pursuant to Article 27 of this Proclamation, and shall be signed by the employer, the employee and, as may be appropriate by the Agency and shall be approved by the labor market information system or the Ministry as may be appropriate.

2/ The employer or the Agency shall, after confirmation by the appropriate authority that the stipulated legal requirements are met, submit the contract to the Ministry.

**46. Deployment of Workers and Reporting**

1/Any Agency shall:

a) deploy the worker within 15 days after the approval of the contract of employment;

b) ensure that the worker deployed to overseas employment has obtained residence permit or obtained a legal document enabling them to reside in the destination country, ensure that the worker obtained work permit, and report the same to the Ministry within 30 days.

https://ethiodata.et/

፪/ መንግስት ከመንግስት እና መንግስት እውቅና ካለው የመዳረሻ ሀገር ድርጅት ጋር ለሚደረግ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ሚኒስቴሩ የላከውን ሠራተኛ በሚሄድበት ሀገር የመኖሪያ ፈቃድ ወይም በመዳረሻ ሀገር ለመኖር የሚያስችል ሕጋዊ ሰነድ እና የሥራ ፈቃድ በአሠሪው አማካኝነት በ፴ ቀናት ውስጥ ስለማግኘቱ ይከታተላል ያረጋግጣል።

፵፯. <u>የሥራ ውልን ስለማሰረዝ</u>

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፮ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ኤጀንሲው ሠራተኛን ወደ ሥራ ማሰማራት ካልቻለ የጸደቀው የሥራ ውል እንዲሰረዝ ከነምክንያቱ እና ማስረጃ በ፴ተከታታይ ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴሩ ማሳወቅ አለበት፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ የቀረበውን የውል ይሰረዝልኝ ጥያቄ መርምሮ በ፭ የሥራ ቀናት ውስጥ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል።

፵፰. <u>ስለ የጋራ እና የተናጠል ኃላፊነት</u>

ከሠራተኛ ጋር የተደረገ የሥራ ውል በአሰሪው ቢጣስ ኤጀንሲውና አሠሪው ለሠራተኛው መብት በጋራና በተናጠል ኃላፊነት ይውሰዳሉ።

2/ Regarding deployment of overseas workers as a result of government to government correspondence, or between government and an agency recognized in the destination country, the Ministry shall follow up that the worker has obtained residence permit or a legal document enabling to reside in the destination country, and ensure that the worker obtained work permit within 30 days.

**47. <u>Revocation of Contract of Employment</u>**

1/ Where the Agency fails to deploy the worker within the time-limit prescribed under Article 46 of this Proclamation, it shall notify, along with the reason and evidence, to the Ministry within one month for the revocation of the approved contract of employment.

2/ The Ministry shall examine the request for revocation and render appropriate decision within five working days.

**48. <u>Joint and Several Liability</u>**

Where the contract of employment of a worker is breached, the Agency and the employer shall be held jointly and severally liable.

https://ethiodata.et/

## ክፍል አምስት

## ስለጥፋት እና ሊወሰድ ስለሚገባው እርምጃ

### ንዑስ ክፍል አንድ

### በኤጀንሲዎች የሚፈጸም ጥፋትና ስለሚወሰዱ እርምጃዎች

**፵፱. አስተዳደራዊ ጉዳዮችን የመወሰን ሥልጣን**

ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን ኤጀንሲው ይህን አዋጅና አዋጁን መሠረት አድርጎ የወጣ ደንብና መመሪያ በመጣሱ ምክንያት የሚነሱ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን የመስማትና የመወሰን ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

**፶. የጥፋት ዓይነቶች እና እርምጃዎች**

፩/ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ የሚያሰጡ የጥፋት ዓይነቶች፡-

ሀ) ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን ቁጥጥር እንዲያካሂድ የመደበውን የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪ ሥራ ማሰናከል ወይም ለማሰናከል መሞከር፤

ለ) በሕግ አግባብ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለስልጣን የሚሰጣቸውን ትዕዛዞችና ማስታወቂያዎች አለመፈጸም እና ሌሎች አሰራሮችን አለመከተል፤

ሐ) ፈቃዱን ሥራውን በሚያካሂድበት ቢሮ ውስጥ ግልጽ ሆኖ ሊታይ በሚችልበት ቦታ አለማኖር፤

፪/ የሚከተሉት ጥፋቶችን ለአንድ ጊዜ መፈጸም የኤጀንሲውን የሥራ ፈቃድ ለሶስት ተከታታይ ወራት ያክል ዕገዳን የሚያስከትሉ ናቸው ፡-

## PART FIVE

## OFFENCES AND CORRESPONDING MEASURE

### SUB-SECTION ONE

### OFFENCES AND CORRESPONDING MEASURES

**49. Power to Decide on Administrative Matters**

The Ministry or the appropriate authority shall have power to hear and decide administrative matters arising out of violations of this Proclamation, and Regulations and Directives issued hereunder.

**50. Type of Offences and Measures**

1/ Offences entailing written warning:

a) obstruction or attempt to obstruct the activities of Labor inspector assigned for the purpose of inspection by the Ministry or appropriate authority;

b) failure to execute legitimate orders and notices given by the Ministry or the appropriate authority, and other working processes in accordance with law;

c) failure to display the license under which it operates in a conspicuous place;

2/ Committing the following offences once shall entail suspension of a license for three consecutive months:

https://ethiodata.et/

ሀ) ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለሥልጣን በቅድሚያ ሳያሳውቅ ሥራ አስኪያጅ ወይም የአመራር ቦርድ አባል መሾም ወይም ሠራተኛ መቅጠር፤

ለ) አግባብ ካለው የምዘና ማዕከል የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ያልያዘ ሠራተኛ ማሰማራት፤

ሐ) ያለበቂ ምክንያት ሠራተኛን በሕጉ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ለሥራ ማሰማራት አለመቻል፤

መ) የላካቸው ሠራተኞች መብት፣ ደህንነት እና ክብር በመጣሱ ምክንያት ለሚቀርበው አቤቱታ መፍትሄ አለመስጠት፤

ሠ) ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን የሚጠይቃቸውን ለሥራ የተሰማሩ ሠራተኞች ወቅታዊ ሪፖርቶች፣ የተገኙ ክፍት የሥራ ቦታዎች፣ በሥራው ምክንያት ከውጭ ሀገር በኮሚሽን መልክ ገቢ የተደረገለትን የውጭ ሀገር ምንዛሪ መጠን በተዘረጋው የአሰራር ስርዓት አለማሳወቅ ወይም ኮሚሽን መቀነስ፤

ረ) በተለያዩ ምክንያቶች ከሥራቸው የተለዩ ሠራተኞች ዝርዝር እና ሌሎች ተመሳሳይ መረጃዎችን በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው ባለሥልጣን የሚጠየቁ መረጃዎችን አለማቅረብ፤

ሰ) በሠራተኛው ባልሆነ ምክንያት ኤጀንሲው ወደ ሥራ ያላሰማራው ሠራተኛ ያወጣውን ወጪ ለሠራተኛው ያለመተካት፤

a) appointing a General Manager or members of the board of directors or recruiting an employee without prior notice to the Ministry or the appropriate authority;

b) deploying a worker who does not possess Certificate of Occupational Competence from an authorized organ;

c) failure, without good cause, to deploy a worker within the legally prescribed time limit;

d) failure to provide remedy for complaints pertaining to violations of workers' rights, safety and dignity;

f) failure to submit periodic reports, through the system established for such purpose, required by the Ministry or the appropriate authority which are related to deployed workers, vacant job positions, foreign currency earned by the Agency in the form of commission for its services and reduction of commission;

g) failure to submit report on the list of workers whose employment is terminated due to various reasons and other similar information requested by the Ministry or the appropriate authority;

h) failure to refund expenses of worker who was not deployed for reason not imputable to him;

https://ethiodata.et/

ሸ) ሠራተኛው ለሥራ በሄደበት ሀገር የአካል ጉዳት ወይም የሞት አደጋ ሲደርስበት የአደጋውን መንስኤና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችን ወዲያውኑ በማጣራት ለሚኒስቴሩ አለማሳወቅ፤

ቀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵ ላይ በተቀመጠው የሥራ ቀናት ውስጥ የቢሮ አድራሻ ለውጥ ለሚመለከታቸው አካላት አለማሳወቅ፤

በ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፮ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከተውን አለመፈጸም፤

ተ) ኤጀንሲው አስፈላጊውን ሂደት አጠናቀው ለበረራ ፵፰ ሰዓት የቀራቸውን፤ ሠራተኞች የምግብና ጊዜያዊ የመጠለያ አገልግሎት አለመስጠት፤

ቸ) ኤጀንሲው አስፈላጊውን ሂደት አጠናቀው ለበረራ ፵፰ ሰዓት የቀራቸውን ሠራተኞች የምግብና ጊዜያዊ የመጠለያ መስጫ ቦታ ውስጥ ተጨማሪ ሠራተኛ ቢገኝ፤

ኀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰውን ጥፋት በ፴ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ከአንድ ግዜ በላይ መፈጸም ናቸው።

፫/ ማንኛውም ኤጀንሲ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው ጥፋት፡-

ሀ) ለሁለተኛ ጊዜ የተፈጸመ ከሆነ ወይም ፪ ጥፋት ከፈጸመ ለስድስት ወር፤

i) failure to immediately verify and report to the Ministry on employment bodily injury sustained by or death of workers on overseas employment together with the reasons thereof and the remedial measure undertaken;

j) failure to notify, to the concerned bodies, the change of office address within the time limit prescribed in Article 40 of this Proclamation;

k) failure to comply with Article 66 (3) of this Proclamation;

l) failure to provide food and temporary shelter for workers who completed all the necessary processes and who are about to fly in 48 hours;

m) having other workers in the premises designated for provision of food and temporary shelter for workers who completed all the necessary processes and who are about to fly in 48 hours;

n) committing the offences mentioned in Sub-Article 1 of this Article more than once within 30 consecutive days;

3/ Any Agency that commits the offences indicated in in Sub-Article (2) of this Article shall have its license suspended as follows:

a) if the offence is committed for a second time, for six (6) months,

https://ethiodata.et/

ለ) ለሦስተኛ ጊዜ የተፈጸመ ከሆነ ወይም ፫ የተለያዩ ጥፋቶች ከፈጸመ ለአሥራ ሁለት ወር፣ ፈቃዱ ይታገዳል፡፡

፬/ የሚከተሉት የፈቃድ ስረዛን የሚያስከትሉ ጥፋቶች ናቸው ፦

ሀ) በግለሰብ የተቋቋመ ኤጀንሲ ወይም ባለቤቱ፣ ሥራ አስኪያጁ ወይም ሠራተኛው በጉዞ ወኪል ወይም የአየር መንገድ ቲኬት ቢሮ ውስጥ በአመራር ወይም በሠራተኛነት፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተሳታፊ ሆኖ መገኘት፤

ለ) ፈቃድ የተሰጠው ኤጀንሲ የተቋቋመው፦

(፩) በሽርክና ወይም ኃላፊነቱ በተወሰነ የግል ማኅበር ከሆነ የማህበሩ አባላት፣ ሥራ አስኪያጁ ወይም ሠራተኛው ፤ ወይም

(፪) በአክሲዮን ማኅበር ከሆነ የማህበሩ የዳይሬክተሮች የቦርድ አባላቱ፣ ሥራ አስኪያጁ ወይም ሠራተኛው፣ በጉዞ ወኪል ወይም የአየር መንገድ ትኬት ቢሮ ውስጥ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በኢሚግሬሽን እና ዜጎች አገልግሎት፣ በኤምባሲዎች በአመራር ወይም በሠራተኛነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተሳታፊ ሆኖ መገኘት፤

ሐ) በዚህ አዋጅ እና ተከትለው በሚወጡ ደንብ እና መመሪያ መሠረት ፈቃድ በወቅቱ አለማሳደስ፤

መ) ዕድሜው ከ፲፰ ዓመት በታች የሆነን ሰው ለሥራ ማሰማራት፤

b) if the offence is committed for a third time, for twelve (12) months.

4/ The following offences shall entail revocation of a license:

a) where an Agency is licensed as sole proprietor, the direct or indirect engagement of the owner, General Manager or employee of the Agency as a manager or as an employee in a travel agency or air ticket office management;

b) for an Agency established in the form of:

(1) partnership or Private Limited Company when its members, General Manager or employee; or

(2) Share Company when its Board of Directors or General Manager or employee engage directly or indirectly in activities a manager or an employee in travel agency or in air ticket office; or directly or indirectly takes part as an administrator or worker in the Ministry of Foreign Affairs, Immigration and Citizenship Service, embassies;

c) failure to timely renew license pursuant to the Overseas Employment Regulation;

d) deployment of a worker who is below the age of eighteen years;

https://ethiodata.et/

ሠ) ፈቃድን በተሳሳተ መረጃ ወይም ሀሰተኛ ማስረጃ በማቅረብ ማግኘት ወይም ማሳደስ፤

ረ) ሠራተኛ ለሥራ እንዳይሰማራ ወደ ተከለከለበት ሀገር ወይም ሠራተኛን ለመላክ ፈቃድ ከተሰጠው ሀገር ውጭ ማሰማራት፤

ሰ) የሕዝብን ጤና ወይም ሞራል በሚጎዳ ወይም የሀገሪቷን ክብርና ገፅታ ለሚያጎድፍ ሥራ ሠራተኛን ማሰማራት፤

ሸ) የተሰጠውን ፈቃድ በዚህ አዋጅ ከተመለከተው ውጭ ለሌላ ማስተላለፍ ወይም ባለቤትነትን መቀየር፤

ቀ) የሥራ ስምሪት አገልግሎትን ምክንያት በማድረግ ከሠራተኛ ገንዘብ በጥሬም ሆነ በዓይነት መቀበል፤

በ) የሥራ ውልን በሚኒስቴሩ ሳያፀድቅ ሠራተኛን ለሥራ ማሰማራት፤

ተ) በሥራ ውሉ ከተመለከተው ሀገር ውጭ ሠራተኛን ለሥራ መላክ፤

ቸ) በተሰጠው ፈቃድ ከተመለከተው የአገልግሎት ዓይነት እና የሥራ ቦታ ውጭ መሥራት፤

ኀ) ሠራተኛን በፀደቀው የሥራ ውል ከተመለከተው አሠሪ ውጭ የሥራ ውሉ ሳይስተካከል ወይም ሳይቀየር ለሌላ አሠሪ ማስተላለፍ፤

ነ) በዚህ አዋጅ፣ በሌላ ሕግ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ በውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት እንዳይሰማራ የተከለከለ ሰው በኤጀንሲው ሥራ ውስጥ እንዲሳተፍ ማድረግ፤

e) obtaining or renewing license based on falsified evidence;

f) deploying a worker to a prohibited destination country or to a destination country other than for which the Agency obtained license;

g) deploying workers to a service that adversely affects public health or morality or tarnishes the country's image;

h) transferring a license or changing ownership in contravention of the provisions of this Proclamation;

i) receiving fee, in cash or in kind, from a worker in return for overseas employment service;

j) deployment of a worker before the approval of the contract of employment by the Ministry;

k) sending a worker to a destination other than what is stipulated in the contract of employment;

l) engaging in a type of service or place of work other than those stipulated in the license;

m) assigning a worker to an employer other than that mentioned in the approved contract of employment without revision or change of the contract;

n) engaging a person, in an Agency's activities, who is prohibited from overseas employment service by this Proclamation, any other law or by a decision of court;

https://ethiodata.et/

ኘ) ሠራተኛን ለሥራ ለማሰማራት ሲባል የተሳሳተ መረጃ ወይም ሰነድ መስጠት ወይም ማስታወቂያ ማውጣት፤

አ) የፀደቀውን የሥራ ውል ሚኒስቴሩን ሳያሳውቅና ሳያፀድቅ በሌላ መተካት ወይም መቀየር፤

ከ) ከምልመላ በፊትም ሆነ የቅድመ ስምሪት ሥራ ተጠናቆ ውል ከፀደቀ በኋላ በማናቸውም ሁኔታ የሠራተኛውን ሕጋዊ የጉዞ ሰነዶችን ይዞ ማቆየት ወይም መከልከል፤

ኸ) ሃሰተኛ የጉዞ ሰነድ ማዘጋጀት ወይም ማቅረብ፤

ዐ) ኤጀንሲው በእጁ የሚገኙ የሠራተኛው ሕጋዊ የጉዞ ሰነዶች ሠራተኛው ሲጠይቅ በሰባት ተከታታይ ቀናት ውስጥ አለመመለስ፤

ዘ) በሥራ ገበያ መረጃ ስርአትን የሚጎዳ ወንጀል መፈጸሙ ሲረጋገጥ፤

ዠ) የሠራተኛውን ደመወዝ ወይም ሠራተኛው ወደ አገሩ የሚልከውን ገንዘብ መያዝ፤

የ) በዚህ አዋጅ የሠራተኛው ወጪዎች ከተባሉት ውጪ ተጨማሪ ክፍያዎችን ማስከፈል፤

ደ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፭ የኮሚሽን ድርድርን በተመለከተ የተቀመጠውን ክልከላ የተላለፈ ፤

ጀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተጠቀሰውን ጥፋት ለአራተኛ ጊዜ መፈጸም፡፡

o) furnishing falsified information or document or advertisement for the purpose of deploying a worker;

p) substituting or replacing the approved contract of employment by another without notifying to and approval of the Ministry;

q) withholding or refusal to handover legal travel documents of the worker before recruitment or after completion of pre-deployment process and approval of the contract;

r) preparing or supplying falsified travel document;

s) failure to return legal travel documents of the worker, upon the request of the worker, within one week;

t) commission of crime on the labor market information system;

u) withholding the salary or remittance of the worker;

v) exacting additional payments other than those recognized by this proclamation as costs imputable to the worker;

w) breach of the restrictions regarding negotiation on Commission as stipulated under Article (25) of this proclamation;

x) commission of the offences stipulated in Sub-Article (2) for the fourth time.

https://ethiodata.et/

፭/ በዚህ አንቀጽ የተዘረዘሩት ጥፋቶችን መፈጸም ከአስተዳደራዊ እርምጃ በተጨማሪ እንደ ሁኔታው አግባብ ባላቸው ሕጎች እና የወንጀል ሕግ ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሰረት የተደነገገውን ተላልፎ የተገኘ አካል አግባብነት ካለው ተቋም ጋር በመተባበር ተገቢውን ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋ'ል።

**፶፩. <u>የፈቃድ መታገድ የሚያስከትለው ውጤት</u>**

፩/ ፈቃዱ የታገደበት ኤጀንሲ ሥራና ሠራተኛ የማገናኘት ተግባሩን ያቆማል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ የኤጀንሲን ፈቃድ ሲያግድ ይህንኑ ለሚመለከታቸው አካላትና ለሕብረተሰቡ አመቺ በሆነ መንገድ ያሳውቃል፡፡

፫/ ፈቃድ የታገደበት ኤጀንሲ የላካቸው ሠራተኞች ከሚያነሱት የመብት ጥያቄ ነፃ አያደርገውም፡፡

፬/ ሚኒስቴሩ የጊዜ ገደቡ በሚጠናቀቅበት ወቅት ለፈቃድ መታገድ ምክንያት የሆነው ጉዳይ የተስተካከለ መሆኑን አረጋግጦ እገዳውን ያነሳል፤ ለፈቃድ መታገድ ምክንያት የሆነው ጉዳይ ባልተስተካከለ ግዜ ፈቃዱን ይሰርዛል።

**፶፪. <u>የፈቃድ መሰረዝ የሚያስከትለው ውጤት</u>**

፩/ ፈቃዱ የተሰረዘበት ኤጀንሲ ሥራና ሠራተኛ የማገናኘት ተግባሩን ያቆማል፡፡

5/ Commission of offences stipulated in this article shall entail, in addition to administrative measures, criminal liability as may be appropriate in accordance with the criminal code.

6/ In collaboration with the appropriate authority, appropriate legal measure shall be taken on anyone who contravenes the stipulation in Sub-Article (5) of this Article.

**51. <u>Consequences of License Suspension</u>**

1/ An Agency whose license has been suspended shall cease to engage in any overseas employment service.

2/ Whenever the Ministry suspends the license of an Agency for any reason; this fact shall be notified to appropriate organs and to the public at large through appropriate means.

3/ Suspension of license does not relieve an Agency from legal claims of workers it sent overseas.

4/ The Ministry shall lift the suspension once it confirms that the issue which led to the license suspension has been rectified by the end of the deadline. If the issue is not rectified within that time, the Ministry will revoke the license.

**52. <u>Consequences of License Revocation</u>**

1/ An Agency whose license has been revoked shall cease to engage in any overseas employment service.

https://ethiodata.et/

፪/ ሚኒስቴሩ የኤጀንሲን ፈቃድ ሲሰርዝ ይህንኑ ለሚመለከታቸው አካላትና ለሕብረተሰቡ አመቺ በሆነ መንገድ ያሳውቃል፡፡

፫/ ፈቃድ የተሰረዘበት ኤጀንሲ የላካቸው ሠራተኞች ከሚያነሱት የመብት ጥያቄ ነፃ አያደርገውም፡፡

፬/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፪ እና ፶፫ ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሥራ ፈቃዱ ሲታገድ ወይም ሲሰረዝ በኤጀንሲው ወደ ውጪ ሀገር ለመላክ በሂደት ላይ ያሉትን ሠራተኞችን በተመለከተ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**፶፫. ስለማቅረብ አቤቱታ**

፩/ ማንኛውም ተጎጂ ሠራተኛ ወይም የተጎጂው ሠራተኛ ህጋዊ ተወካይ ወይም የተጎጂ ሠራተኛ ቤተሰብ ይህን አዋጅ እና በአዋጁ መሠረት የወጣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ሌላ ተዛማጅነት ያለው ሕግ በኤጀንሲው ተጥሷል በሚል በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለሥልጣን አቤቱታ በጽሁፍ ወይም በቃል ማቅረብ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት አቤቱታው የቀረበው በቃል ከሆነ የሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን ኦፊሰር አቤቱታውን በወረቀት ላይ በማስፈር አቤቱታ አቅራቢው እንዲፈርም ማድረግ አለበት፡፡

፫/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን በራሱ ተነሳሽነት ወይም በሌላ አካል የሚቀርብለትን በዚህ አዋጅ የተመለከተውን የሕግ ጥሰት የሚመለከት ሪፖርት መሠረት በማድረግ ጉዳዩ እንዲታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

2/ Whenever the Ministry revokes the license of any Agency for any reason, this fact shall be notified to appropriate organs and to the public at large through appropriate means.

3/ Revocation of license does not relieve an Agency from legal claims of workers it deployed overseas.

4/ Notwithstanding the provisions of Articles 52 and 53 of this Proclamation, a suspended or revoked agency shall transfer workers who are in the process of overseas employment to other active agencies, with the details to be determined by a Directive.

**53. Submission of Complaint**

1/ Any victim worker or his legal representative or family member may submit oral or written complaint to the Ministry or the appropriate authority when this Proclamation, or any regulation or directive issued hereunder, or any other relevant law has been contravened by an Agency.

2/ If the complaint pursuant to Sub-Article (1) of this Article is submitted orally, the officer of the Ministry or the appropriate authority shall reduce it in writing and cause the complainant to sign.

3/ The Ministry or the appropriate authority may conduct proceedings on its own initiative or based on complaints received from other bodies on the violation of the provisions of this Proclamation.

https://ethiodata.et/

፬/ ለዚ አንቀጽ ቤተሰብ ማለት የትዳር ጓደኛ፣ ወላጅ፣ተወላጅ፣የጉዲፈቻ ልጅ ወይም እስከ ሁለተኛ ደረጃ ድረስ የሚቆጠር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመድ ነው።

## ፶፬. የአቤቱታ ይዘት

በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፶፫ መሠረት የሚቀርብ አቤቱታ ሌሎች ተጨማሪ ዝርዝር መግለጫዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፦

፩/ የአቤቱታ አቅራቢ ስም እና አድራሻ፤
፪/ አቤቱታ የቀረበበት ኤጀንሲ ስም እና አድራሻ፤
፫/ የአቤቱታው ዓይነት፣ ፍሬ ጉዳይ እና ምክንያት፤
፬/ ለአቤቱታው ምክንያት የሆነው ድርጊት የተፈፀመበት ጊዜና ቦታ፤
፭/ በአቤቱታው የተጠየቀ ገንዘብ ካለ መጠኑ፤
፮/ የተጠየቀው መፍትሔ፤
፯/ ሌሎች አግባብነት ያላቸው ደጋፊ ማስረጃዎች፡፡

## ፶፭. አቤቱታ ስለመስማት

፩/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፶፫ እና ፶፬ መሠረት አቤቱታ ሲቀርብ ፋይል ይከፍታል፤ይመረምራል።

፪/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን አቤቱታ እንደደረሰው የአቤቱታውን ቅጂና ደጋፊ ሰነዶች በማያያዝ አቤቱታ የቀረበበት ኤጀንሲ እንደ ጉዳዩ ዓይነት ከ፫ እስከ ፯ የስራ ቀናት ውስጥ መልሱን እንዲያቀርብ የመጥሪያ ትዕዛዝ ይሰጣል።

4/ In this Article, "family" refers to a spouse, parent, descendant, adopted child, or a blood or marriage relative up to the second degree of consanguinity or affinity.

## 54. Content of Complaint

The complaint to be submitted pursuant to Article (53) of this Proclamation shall, among other details, include the following:

1/ Name and address of the complainant;
2/ Name and address of the Agency against whom a complaint was submitted;
3/ Nature of the complaint, relevant facts and reasons for the complaint;
4/ Time and place of the commission of the act complained;
5/ The amount of money claimed, if any;
6/ Relief sought;
7/ Other relevant supportive evidence.

## 55. Complaint Hearing

1/ The Ministry or the appropriate authority shall open a file to a complaint submitted to it pursuant to Article (53) and (54) of this Proclamation and proceed for examining and hearing of the case.

2/ The Ministry or the appropriate authority shall, upon receipt of the complaint, issue summons order, together with the copy of the compliant and supporting documents, directing the respondent Agency to present its statement of defense within three to seven working days, depending on the nature of the case.

https://ethiodata.et/

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በመጥሪያ ለደረሰው አቤቱታ ኤጀንሲው መልስ ካልሰጠ መልስ ሰጭ በሌለበት አቤቱታ የመስማት ሂደት ይቀጥላል።

፬/ አቤቱታ አቅራቢው ያቀረበውን አቤቱታ በማናቸውም ምክንያት ቢያቋርጥ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን ጉዳዩን በመመርመር ተገቢውን ውሳኔ ከመስጠት አያግደውም።

፭/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን የቀረበለትን አቤቱታ በማጣራትና በመመርመር አቤቱታው በቀረበ በ፲፭ የስራ ቀናት ውስጥ ለጉዳዩ ውሳኔ ይሰጣል።

፮) በምርመራ ሂደት የወንጀል ፍሬ ከተገኘ ለሚመለከተው አካል ይልካል።

## ፶፮. ጊዜያዊ እርምጃ ስለመውሰድ

ሚኒስቴሩ፡-

፩/ ይህን አዋጅ፣ አዋጁን መሠረት አድርጎ የወጣ ደንብ ወይም መመሪያ በመጣሱ ምክንያት የቀረበለትን አቤቱታ አጣርቶ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ በተጠሪው ኤጀንሲ በኩል የሚቀርብን የሥራ ውል አያፀድቅም፤

፪/ አቤቱታ በማጣራትና በመመርመር አቤቱታው በቀረበ በ፲፭ የስራ ቀናት ውስጥ ለጉዳዩ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ በሚከተሉት ምክንያቶች የኤጀንሲውን ፈቃድ አግዶ ያቆያል፡-

ሀ) አቤቱታ የቀረበበት ኤጀንሲ በአካል እንዲቀርብ ወይም አስፈላጊውን ሰነድ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ደርሶት ይህንኑ ካልፈፀመ፤

3/Where the respondent Agency fails to submit its statement of defense, after having received the summon pursuant to Sub-Article (2) of this Article, the proceeding shall resume ex-parte.

4/ Withdrawal of complainant by the complainant for whatever reason shall not bar the Ministry or the appropriate authority from proceeding with the case and passing decision.

5/ The Ministry or the appropriate authority shall render its decision within 15 working days by investigating and examining the complaint submitted to it.

6/ Where the investigation reveals criminal elements, it shall be reported to the concerned body.

## 56. Temporary Measure

The Ministry shall:

1/ Not approve any contract of employment submitted by the respondent Agency until the complaint instituted on violation of this Proclamation, Regulation and Directives issued hereunder has been examined and determined;

2/ Suspend the respondent Agency's license within 15 working days after the filing of the complaint and this will remain in effect until the complaint is disposed of on the following grounds:

a) if the Agency against which a complaint is lodged fails to appear in person or fails to present the relevant document after receiving order to that effect;

https://ethiodata.et/

ለ) ኤጀንሲው ሥራውን ቢቀጥል በሚመለምላቸው ሠራተኞች ላይ የከፋ የመብት ጥሰት ወይም ብዝበዛ የሚያስከትል ወይም ከማንኛውም ሀገር ጋር ያለውን ግንኙነት የሚጎዳ ወይም የሀገርን ጥቅም የሚፃረር ድርጊት ለመኖሩ አሳማኝ ከሆነ፤

ሐ) ይህን አዋጅ፣ አዋጁን መሠረት አድርጎ የወጣ ደንብ ወይም መመሪያ በተጠሪው ኤጀንሲ ስለመጣሱ የሚያስረዳ ማስረጃ ከቀረበ፡፡

**፶፯. የውሳኔው ይዘት**

ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ(፭) መሠረት የሚሰጠው ውሳኔ ግልፅና አጭር ሆኖ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፦

፩/ የጉዳዩን ፍሬ ነገር፤

፪/ የጉዳዩን ጭብጥ፤

፫/ የቀረቡ ማስረጃዎች፤

፬/ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ፤

፭/ ምክንያቶቹ እና ማጠቃለያ፤ የተሰጠ ውሳኔ፡፡

**፶፰. የአፈፃፀም ትዕዛዝ ስለመስጠት**

፩/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለ ሥልጣን በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት የሰጠውን ውሳኔ ኤጀንሲው እንዲፈጽም ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሰጠውን ትዕዛዝ አቤቱታ የቀረበበት ኤጀንሲ በ፲፭ ተከታታይ ቀናት ውስጥ የመፈፀም ግዴታ አለበት።

b) if it is believed that the continued operation of the Agency may lead to further violation or exploitation of workers to be recruited or adversely affect relations with any country or prejudice national interest;

c) if there is prima facie evidence of a case for violation of this Proclamation, Regulations or Directive issued hereunder.

**57. Content of the Decision**

The decision of the Ministry or the appropriate authority rendered in accordance with Article 55 (5) of this Proclamation shall be precise and short, and shall contain the following:

1/ Material facts;

2/ Issue framed;

3/ provided evidences;

4/ Laws, Regulations or Directives relevant to the issue;

5/ Reasoning and conclusion; the decision rendered.

**58. Issuance of Execution Order**

1/ The Ministry or the appropriate authority shall issue an execution order to the respondent Agency to execute its decision rendered in accordance with Article 55(5) of this Proclamation.

2/ The respondent Agency shall, within 15 consecutive days, execute the order of the Ministry or the appropriate authority issued pursuant to Sub-Article (1) of this Article.

https://ethiodata.et/

**፶፱. የውሳኔ አፈፃፀም ቅደም ተከተል**

በዚህ አዋጅ መሠረት የሠራተኛ ስምሪት ሥርዓት ጥሰት በመፈፀሙ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው ባለሥልጣን ወይም የሥራ ክርክር ለማየት ሥልጣን በተሰጠው አካል የተወሰነን ውሳኔ በሚመለከት የተሰጠን የአፈፃፀም ትዕዛዝ ኤጀንሲው ካልፈፀመ ውሳኔው በሚከተለው ቅደም ተከተል ተፈፃሚ ይሆናል ፦

፩/ ኤጀንሲው ለሠራተኞች ዋስትና ማስከበሪያ በዝግ ሂሳብ በባንክ ባስቀመጠው ገንዘብ፤

፪/ ኤጀንሲው የግል ድርጅት ከሆነ በሚንቀሳቀስ የግል ንብረት ላይ ወይም ኤጀንሲው የንግድ ማኅበር ከሆነ በሚንቀሳቀስ የማኅበሩ ንብረት ላይ፤

**ንዑስ ክፍል ሁለት**
**በአሠሪ፣ በኤጀንሲ ወኪል ወይም በሠራተኛ የሚፈፀም ጥፋትና የሚወሰድ ዕርምጃ**

**፷. በአሠሪ ወይም በኤጀንሲ ወኪል ስለሚፈፀሙ ጥፋቶች**

፩/ በአሠሪ ላይ አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ የሚያበቁ ጥፋቶች የሚከተሉት ናቸው፦

ሀ) በገባው የሥራ ውል መሠረት ግዴታውን አለመወጣት፤

ለ) የሠራተኛን ሕጋዊ የጉዞ ሰነዶች በማናቸውም ምክንያት መያዝ ወይም እንዳያገኝ መከልከል፤

**59. Sequence of Execution of Decision**

When an Agency held liable for contravening workers the deployment process prescribed under this Proclamation, by the decision of Ministry or the appropriate authority or the organ empowered to entertain labor disputes but fails to execute the decision, the execution shall be applied in accordance with the following sequence:

1/ Over the Agency's blocked account allocated for the overseas workers' security bond;

2/ Over the Agency's movable property if the Agency is sole proprietor or over the movable property of the business organization if the Agency is a business organization;

**SUB-SECTION TWO**
**OFFENCES COMMITTED BY AN EMPLOYER, AN AGENCY'S REPRESENTATIVE AND WORKERS AND THE CORRESPONDING MEASURES**

**60. Offences Committed by Employer and Representative of an Agency**

1/ The following violations shall suffice to impose appropriate measure against employer or representative of an Agency:

a) failure to discharge its obligation as agreed in the contract of employment;

b) withholding or denying access to the worker's legal travel documents for whatever reasons;

https://ethiodata.et/

ሐ) የሠራተኛን ደመወዝ ወይም ሠራተኛው ወደ ሀገር የሚልከውን ገንዘብ ያለበቂ ምክንያት መያዝ፤

መ) በሠራተኛው ላይ ከባድ ጉዳት፣ ህመም ወይም የሞት አደጋ ማድረስ፤

ሠ) የሠራተኛውን ሰብዓዊ ክብርና ሞራል የሚነካ ድርጊት መፈጸም፤

ረ/ በሠራተኛው ላይ ጾታዊ ጥቃት መፈጸም፤

ሰ) ሚኒስቴሩ ከመዳረሻ ሀገር ጋር ያደረገውን የሁለትዮሽ ስምምነት ወይም የመግባቢያ ሰነድ መጣስ፤

ሸ) ይህን አዋጅ፣ አዋጁን ለማስፈጸም የወጣ ደንብ ወይም መመሪያን መጣስ፡፡

፪/ በኤጀንሲ ወኪል ላይ አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ የሚያበቁ ጥፋቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ) በውክልናው መሠረት ግዴታውን አለመወጣት፤

ለ) በአሠሪው የሚደርስ ማንኛውም የመብት ጥሰት ላይ ሠራተኛው ተገቢውን ካሳ እንዲያገኝ አለማድረግ፤

ሐ) ሠራተኛው ወደ ሥራ እስከሚሰማራ ድረስ አስፈላጊውን የምግብ የመጠጥ እና የመጠለያ አገልግሎት አለማሟላት፤

መ) ለኢትዮጲያ ኤጀንሲዎች የሥራ ትዕዛዝ ሰጥቶ ግልጽ ባልሆነ ምክንያት ትዕዛዙን ሲሰርዝ ይህም በማስረጃ ሲረጋገጥ፤

ሠ)ይህን አዋጅ፣ አዋጁን ለማስፈጸም የወጣ ደንብ ወይም መመሪያን መጣስ፡፡

c) withholding, without good cause, the workers wage or his remittances;

d) causing serious injury, health problem or death on the worker;

e) committing an act that affects worker's human dignity and moral;

f) commission of sexual harassment on the worker;

g) violation of the provision of the bilateral agreement or the memorandum of understanding with the destination country;

h) violation of this Proclamation, regulations or directives issued hereunder.

2/ The following violations shall suffice to impose appropriate measure against the representative of an Agency:

a) failure to discharge its obligation in accordance with the authorization in delegation.

b) failure to ensure that the employer makes good any damage that ensue to the worker due to breach of the worker's right.

c) failure to provide the necessary food, drinks, and shelter until the deployment of the worker.

d) cancelling a work order addressed to the Ethiopian Agency for unknown reason and this is ascertained.

e) violation of this Proclamation, Regulations or Directives issued hereunder.

https://ethiodata.et/

**፷፩. በአሠሪ ወይም በኤጀንሲ ወኪል ላይ የአቤቱታ አቀራረብና ውሳኔ አሰጣጥ**

፩/ ተጎጂ ሠራተኛ ወይም ማንኛውም ሰው በአሠሪው ወይም በኤጀንሲ ወኪል ጥፋት ተፈጽሟል በሚል አቤቱታ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለሥልጣን ማቅረብ ይችላል፣

፪/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን በራሱ ተነሳሽነት ወይም በሌላ አካል የሚቀርብለትን በዚህ አዋጅ የተመለከተውን የሕግ ጥሰት የሚመለከት ሪፖርት መሠረት በማድረግ ጉዳዩ እንዲታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፫/ አቤቱታ የቀረበበት አሠሪ ወይም የኤጀንሲ ወኪል ጉዳዩ ታይቶ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ከኢትዮጵያ ሠራተኛ እንዳይቀጥር ወይም በውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት እንዳይሳተፍ ለጊዜው በሚኒስቴሩ ሊታገድ ይችላል።

፬/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን የቀረበለትን አቤቱታ በማጣራት እና በመመርመር አቤቱታው በቀረበ በ፲፭ የሥራ ቀናት ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**፷፪. የአቤቱታ ይዘት**

በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፷፩ (፩) እና (፪) መሠረት የሚቀርብ ማንኛውም አቤቱታ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል ፦

፩/ የአቤቱታ አቅራቢው ስም እና አድራሻ፤

፪/ አቤቱታ የቀረበበት አሠሪ ወይም የኤጀንሲ ወኪል ስም እና አድራሻ፤

፫/ የተፈጸመ ጥፋት ዓይነት፤

**61. Complaint Procedure against an Employer or a Representative Agency and the Decision Making**

1/ A victim worker or any person may submit a complaint to the Ministry or the appropriate authority alleging the commission of offence by employer or a representative of Agency.

2/ The Ministry or the appropriate authority may conduct proceedings on its own initiative or based on reports received from other body concerning violation of the provisions of this Proclamation.

3/ An employer or a representative of an Agency against whom a complaint has been lodged may be suspended from employing worker from Ethiopia or participating in overseas employment service until the complaint is disposed of.

4/ The Ministry or the appropriate authority shall render decision within 15 working days by investigating and examining the complaint submitted to it.

**62. Content of the Complaint**

Any complaint submitted pursuant to Article 61 (1) and (2) of this Proclamation shall contain the following information:

1/ The name and address of the complainant;

2/ The name and address of the employer or a representative of an Agency against whom complaint is lodged;

3/ The nature of the offence committed;

https://ethiodata.et/

፬/ ጥፋቱ የተፈፀመበት ጊዜና ቦታ፤

፭/ ሌሎች ደጋፊ ማስረጃዎች፡፡

፷፫. <u>ውሳኔው የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት</u>

አቤቱታ የቀረበበት አሠሪ ወይም የኤጀንሲ ወኪል ጥፋት መፈጸሙ በሚኒስቴሩ ከተረጋገጠ፦

፩/ አሠሪው ከኢትዮጵያ ውስጥ ሠራተኛን ለመቅጠር አይፈቀድለትም፤

፪/ የኤጀንሲው ወኪል በኢትዮጵያ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ተግባር ሊሳተፍ አይችልም፤

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷ መሠረት በተፈፀመው ጥፋት ምክንያት በሠራተኛው ላይ ለደረሰ ጉዳት አሠሪው ወይም የኤጀንሲው ወኪል ተመጣጣኝ ካሣ ይከፍላል፡፡

፬/ ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ አንቅጽ ፷ ስር የተዘረዘሩ ጥፋቶች በቀጣሪው ወይም በወኪል ኤጀንሲው መፈጸሙ ሲያረጋግጥ በተቀባይ ሃገር ጋር በተፈራረመው የሁለትዮሽ ስምምነት ወይም የመግባቢያ ሰነድ መሰረት በተቀባይ ሃገር መንግስት እና ህግ መሰረት የሚጠየቅበትን መንገድ ያመቻቻል።

፷፬. <u>በሠራተኛ ስለሚፈፀሙ የጥፋት ዓይነቶች</u>

፩/ የሚከተሉት ጥፋቶች በሠራተኛ ላይ አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ የሚያበቁ ናቸው ፦

ሀ) በገባው የሥራ ውል መሠረት ግዴታውን አለመወጣት፤

4/ The time and place of the offence committed;

5/ Other supportive evidence.

63. <u>Legal Consequence of the Decision</u>

Where the Ministry or the appropriate authority ascertains that the employer or a representative of Agency has committed the offence reported:

1/ The employer shall be prohibited from employing workers from Ethiopia;

2/ The representative of the Agency shall be prohibited from participating in the Ethiopian overseas employment activity;

3/ The employer or the representative of the Agency shall be liable to pay adequate compensation for the offence it committed as stipulated in Article 60 of this Proclamation.

4/ Where it is ascertained that the offences stipulated in Article 60 of this Proclamation are committed by the employer or a representative of Agency, the minister shall facilitate, pursuant to the bilateral agreement or memorandum of association with the destination country, accountability by the government of the destination country in accordance its law.

64. <u>Types of Offences Committed by a Worker</u>

1/The following offences shall suffice to impose appropriate measures against worker:

a) failure to discharge his obligation as agreed in the contract of employment;

https://ethiodata.et/

ለ) በኢትዮጵያ ወይም በተቀባይ ሀገር ባሉ ሕጎች በወንጀል የሚያስቀጣ ድርጊት መፈፀም፤

ሐ) የተቀባይ ሀገር እምነት፣ ባህል እና ልማድን የሚፃረር ድርጊት መፈፀም፤

መ) አግባብ ባለው የመንግሥት አካል የሥራ ውሉ ከፀደቀ በኋላ ያለበቂ ምክንያት በሥራ ላይ ለመሰማራት ፈቃደኛ ሆኖ አለመገኘት፤

ሠ) የአሠሪን ወይም አብሮ የሚሰራ ሠራተኛን ገንዘብ ወይም ንብረት ያለአግባብ መጠቀም፣ መውሰድ፤

ረ) ከውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ጋር በተያያዘ የተሳሳተ መረጃ ማቅረብ፤

ሰ/ ከሕግ ውጪ የሥራ ውልን ማቋረጥ፤

ሸ) የተቀጠረበትን የሥራ ቦታ ሕጋዊ አግባብን ባልጠበቀ መንገድ ትቶ መሄድ ወይም መጥፋት ፤ ወይም

ቀ) ሌሎች ተመሳሳይነት ያላቸው ጥፋቶችን መፈጸም።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን አንዱን ጥፋት የፈፀመ ማንኛውም ሠራተኛ፦

ሀ) ጥፋቱን የፈፀመው ለመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ ከውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ዕድል ለአንድ ዓመት ጊዜ ይታገዳል፤

ለ) ጥፋቱን የፈፀመው ለሁለተኛ ጊዜ ከሆነ ከውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ዕድል ለሁለት ዓመት ጊዜ ይታገዳል፤

b) commission of crimes punishable in Ethiopia or in the country of destination;

c) commission of an act that contravenes the religion, custom or traditional practice of the country of destination;

d) unwillingness to be deployed, without good cause, after the contract of employment has been approved by the Ministry;

e) unauthorized use or taking of employers' or colleagues' money or property;

f) provision of false information in connection with overseas employment;

g) terminating contract of employment without good cause;

h) deserting from the place of employment without complying with legal requirements or ,

i) commission of other similar offences.

2/ Without prejudice to the liability of the worker in accordance with other relevant laws for the contravention of Sub-Article (1) of this Article, the following measures shall apply:

a) if the offence is committed for the first time, the worker shall be suspended from overseas employment for one year;

b) if the offence is committed for the second time, the worker shall be suspended from overseas employment for two years;

https://ethiodata.et/

ሐ) ጥፋቱን የፈፀመው ለሦስተኛ ጊዜ ከሆነ ለውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ብቁ አይሆንም፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተውን ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ጥፋቶችን በአንድ ግዜ ወይም በተለያየ ጊዜ የፈፀመ ማንኛውም ሠራተኛ አግባብ ባለው ሕግ ተጠያቂ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፦

ሀ) ጥፋቱን የፈፀመው ለመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ ከውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ዕድል ለሁለት ዓመት ጊዜ ይታገዳል፣

ለ) ጥፋቱን የፈፀመው ለሁለተኛ ጊዜ ከሆነ ለውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ብቁ አይሆንም፡፡

## ፷፭. ለፍርድ ቤት አቤቱታ የማቅረብ መብት

፩/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን ይህን አዋጅ ወይም በአዋጁ መሠረት የወጣ ደንብ ወይም መመሪያ በመተላለፍ በሚፈፀመው ጥፋት ላይ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔው በደረሰው በ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም በክልል ሥልጣን ለተሰጠው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዐስ አንቀጽ (፩) መሠረት በፍሬ ነገር ክርክር ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ወይም በክልል ሥልጣን ለተሰጠው ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

c) if the offence is committed for the third time, the worker shall be disqualified from overseas employment;

3/ Without prejudice to the liability of the worker in accordance with other relevant laws, commission of two or more of offences stipulated in Sub-Article (1) of this Article at a time or at different times, the following measures shall apply:

a) if the offence is committed for the first time, the worker shall be suspended from overseas employment for two years;

b) if the offence is committed for the second time, the worker shall be disqualified from overseas employment;

## 65. Right to Lodge Pleading before Court of Law

1/ A party aggrieved by the decision of the Ministry or the appropriate authority in connection with the violation of this proclamation, Regulations and Directives issued thereto may, within 15 working days, lodge his appeal to the Federal High Court or a regional court having jurisdiction.

2/ The decision given by the Federal High Court or a regional court having jurisdiction pursuant to Sub-Article (1) of this Article shall be final regarding issues of fact.

https://ethiodata.et/

## ክፍል ስድስት
## ስለማህበራዊ ደህንነት አገልግሎት
## ንዑስ ክፍል አንድ
## ስለዋስትና ገንዘብና ኢንሹራንስ

**፷፮. ስለዋስትና ገንዘብ**

፩/ ማንኛውም ኤጀንሲ ለሠራተኛው መብት ክብር እና ደህንነት ዋስትና ማስከበሪያ የሚውል ገንዘብ በዶላር ወይም ተመጣጣኙን የኢትዮጵያ ብር በሚኒስቴሩ ለዚሁ ዓላማ በተከፈተ የባንክ የሂሳብ ቁጥር ማስቀመጥ አለበት፡፡

ሀ)ኤጀንሲዎች ደረጃ ፩ $ ፪፻፶ሺ (ሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ የአሜሪካን ዶላር)፣

ለ)ደረጃ ፪ $ ፪፻ሺ (ሁለት መቶ ሺህ የአሜሪካን ዶላር)፣

ሐ) ደረጃ ፫ $ ፩፻፶ሺ(አንድ መቶ ሀምሳ ሺ የአሜሪካን ዶላር)፣

መ) ደረጃ ፬ $ ፩፻ሺ (አንድ መቶ ሺህ የአሜሪካን ዶላር)፣

ሠ) ደረጃ ፭ $ ፶ሺ (ሃምሳ ሺህ የአሜሪካን ዶላር)፣

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፸፮ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) የተመለከተውን ኤጀንሲው ካልፈጸመ ሚኒስቴሩ ተቀማጭ ከሆነው የዋስትና ገንዘብ ላይ ወጪ በማድረግ ለሠራተኛው መብት ክብር እና ደህንነት ዋስትና ማስከበሪያ ያውላል፡፡

## PART SIX
## WELFARE SERVICE
## SUB-SECTION ONE
## FINANCIAL GUARANTEE AND INSURANCE

**66. Financial Guarantee**

1/ Any Agency shall deposit money, in USD or its equivalent in Birr, in a bank account opened for this purpose by the Ministry to guaranteeing the protection of the right, dignity and safety of deployed workers. The amount of guarantee agencies must deposit, according to their respective levels, shall be as follows:

a) 1st level agencies, $250,000 (Two Hundred Fifty Thousand USD),

b) 2nd level agencies, $200,000 (Two Hundred Thousand USD),

c) 3rd level agencies, $150,000 (One Hundred Fifty Thousand USD) ,

d) 4th level agencies, $100,000 (One Hundred Hhousand USD),

e) 5th level agencies, $50,000 (Fifty Thousand USD),

2/ Where the Agency fails to execute the duty imposed on it pursuant to paragraph (a) and (b) of Article 76(1) of this Proclamation, the Ministry is empowered to withdraw the required amount from the deposited money and use it for as a security for the protection of the right, dignity and safety of the worker.

https://ethiodata.et/

፫/ ተቀማጭ የሆነው የዋስትና ገንዘብ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፱ (፩) እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(፪) መሠረት በጥቅም ላይ ከዋለ ኤጀንሲው ተቀናሽ የሆነውን የዋስትና ገንዘብ መጠን በ፲ የሥራ ቀናት ውስጥ መልሶ መተካት ይኖርበታል፡፡

፬/ ኤጀንሲው በማናቸውም ሁኔታ ሥራውን ሲያቆም ሚኒስቴሩ የዋስትናውን ገንዘብ የሚለቀው ከሠራተኛ መብትና ጥቅም ጋር የተያያዘ ጥያቄ ሥልጣን በተሰጠው አካል በመታየት ላይ ካልሆነ እና በኤጀንሲው አማካይነት ለሥራ ወደ ውጭ ሀገር የተላኩ ሠራተኞች በሙሉ የሥራ ውላቸው ከተቋረጠ ከ፮ ወር በኋላ እንዲሁም የላካቸው ሠራተኞች ያሉበትን ነባራዊ ሁኔታ የሚያሳይ ሪፖርት ሲያቀርብ ነው።

፭/ ሚኒስቴሩ የዋስትና ገንዘብ አፈፃፀምን በተመለከተ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል።

## ፷፯. የውጭ አሠሪዎች ዋስትና ፈንድ

፩/ በሚኒስቴሩ አማካኝነት ሠራተኛን የሚቀጥር ማንኛውም የውጭ ሀገር መንግሥታዊ ድርጅት ወይም የግል ድርጅት ሆነ ቀጥታ ቅጥር የተፈቀደለት ማንኛውም የውጭ ሀገር አሠሪ የሚቀጥራቸው ሠራተኞች ከሥራ ውል ጋር በተያያዘ የሚያነሱትን የገንዘብ ጥያቄዎች መሸፈን እንዲቻል የውጭ አሠሪዎች የዋስትና ፈንድ በዚህ አዋጅ መሠረት ተቋቁሟል፡፡

3/ Where the deposited amount has been used pursuant to Article 59 (1) of this Proclamation and Sub-Article (2) of this Article, the Agency shall replenish the fund within 10 working days.

4/ Whenever the Agency ceases operation in whatsoever situation, its financial guarantee shall be released by the Ministry when there is no pending claim against the Agency before any competent organ and after six months from the termination of the employment contracts of all workers who were deployed overseas by the Agency, and after submission of a report showing the status of workers deployed abroad by the Agency.

5/ The Ministry shall determine detailed matters related to the administration of the guarantee fund through a Directive.

## 67. Foreign Employers' Guarantee Fund

1/ A Foreign Employers' Guarantee Fund is hereby established for the purpose of securing monetary claims, that may arise from breach of contract of employment, of workers employed through the Ministry by a foreign Governmental Organizations or company as well as workers of a foreign employer who has been allowed for direct employment.

https://ethiodata.et/

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሰረት በሚኒስቴሩ አማካኝነት ሠራተኛን የሚቀጥር ማንኛውም የውጭ ሀገር መንግሥታዊ ወይም የግል ድርጅት ሆነ ቀጥታ ቅጥር የተፈቀደለት ማንኛውም አሠሪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሥር ለተጠቀሰው ዓላማ የሚውል ለሚቀጥረው ለእያንዳንዱ ሠራተኛ አንድ መቶ (፻) የአሜሪካን ዶላር በአዋጁ መሠረት ለተቋቋመው የውጭ አሠሪዎች ዋስትና ፈንድ መዋጮ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፫/ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም የውጭ ሀገር አሠሪ በሥራ ውል መጣስ ምክንያት ለሚደረግ ክፍያ የሚውል ለውጭ አሠሪዎች ዋስትና ፈንድ የሚያስገባው የመዋጮ መጠን እንደገበያው ሁኔታ እየታየ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

፬/ የዋስትና ፈንዱ በማናቸውም የዕዳ ክፍያ ምክንያት መያዣ ወይም ማቻቻያ ሊሆን አይችልም፡፡

፭/ ሚኒስትሩ ስለሚቋቋመው የውጭ አሠሪዎች ዋስትና ፈንድ የገንዘብ አቀማመጥ እና ዝርዝር አፈፃፀም በመመሪያ ይወሰናል።

## ፷፰. የሠራተኞች ዋስትና ፈንድ

ማንኛውም ሠራተኛ ከሚያገኘው ገቢ ላይ ለዋስትና ፈንድ የሚሆን ገንዘብ ለተቋቋመው የሠራተኞች ዋስትና ፈንድ መዋጮ ሊያደርግ ይችላል።

## ፷፱. ስለኢንሹራንስ ሽፋን

፩/ ማንኛውም ለሥራ ወደ ውጭ ሀገር ለሚሄድ ሠራተኛ አሠሪው የሕይወትና የአካል ጉዳት ካሳ ኢንሹራንስ ሽፋን በሀገር ውስጥ የመግባት ግዴታ አለበት፡፡

2/ The foreign employer, be it a foreign Governmental Organizations or company or a foreign employer who has been allowed for direct employment, who employs workers through the Ministry as specified under Sub-Article (1) of this Article shall deposit one hundred (100) USD for each worker it recruits to Foreign Employers' Guarantee Fund which shall be used for the purpose stipulated in sub-article 1 of this article.

3/ Notwithstanding the stipulation under Sub-Article (1) of this Article, the amount to be deposited by the foreign employer for the purpose of securing payments arising from breach of employment contract may be amended by the Ministry in line with the market situation.

4/ The Guarantee Fund may not be attached or used for set off for whatever claim.

5/ The Ministry shall determine the detailed matters related to the implementation of the guarantee fund through a Directive.

## 68. Workers' Welfare Fund

Any worker may contribute from his income to the established workers' welfare fund.

## 69. Insurance Coverage

1/ The employer shall, from the domestic insurance market, buy life and disability insurance for any worker deployed overseas.

https://ethiodata.et/

፪/ ኤጀንሲ፣ አሠሪ ወይም ሠራተኛ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ሰነዱን ከሥራ ውል ጋር አያይዞ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ አለበት።

፸. ስለ ኮሚሽን

፩/ ሚኒስቴሩ የዜጎችን መብት እና ተጠቃሚነት እንዲሁም የሀገርን ጥቅም ለማስከበር ኤጀንሲዎች ከተቀባይ ሀገር ኤጀንሲዎች ጋር የሚያደርጉትን የኮሚሽን መጠን ድርድር ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ዝቅተኛውን የኮሚሽን ዋጋ ያስቀምጣል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ድጋፍም ያደርጋል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ (፩) ላይ የተቀመጠውን የኮሚሽን ድርድር ማድረግ የሚችለው የኤጀንሲዎች ፌዴሬሽን ሆኖ ሚኒስቴሩ ከድርድሩ በፊት እውቅና መስጠት ይኖርበታል።

፫/ ማንኛውም ኤጀንሲ ሠራተኛን ከሚያሰማራበት እያንዳንዱ መዳረሻ ሀገር ኤጀንሲ ጋር የሚያደርገውን የኮሚሽን ስምምነት ሰነድ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ አለበት።

፬/ ኤጀንሲዎች በእያንዳንዱ ሠራተኛ ምክንያት ያገኙትን የኮሚሽን መጠን ለሚኒስቴሩ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

፭/ ሚኒስቴሩ ከውጭ ሃገር የሥራ ስምሪት ጋር በተያያዘ ኤጀንሲዎች የሚያገኙትን ኮሚሽን በህጋዊ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ ስለመግባቱ ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር ያደርጋል።

2/ An Agency, the employer or the worker shall present to the Ministry the insurance policy document accompanied by contract of employment.

**70. Commission**

1/ To safeguard the rights and interests of citizens and the national interest, the Ministry shall monitor and supervise the negotiation on commission between domestic Agencies and Agencies in the receiving countries, determine the minimum amount of commission and provide support as needed.

2/ Negotiation on commission pursuant to Sub-Article (1) of this Article shall be undertaken by the federation of Agencies with prior approval of the Ministry.

3/ Any Agency shall submit the commission agreement it entered with the Agencies of each destination country where it deploys workers.

4/Agencies shall submit to the Ministry evidence of the commission earned from each worker.

5/ The Ministry shall properly follow up and monitor that the commission earned by Agencies in connection with overseas deployment of workers is legally remitted to Ethiopia.

https://ethiodata.et/

፮/ ለኤጀንሲዎች የሚከፈል የኮሚሽን መጠን እንደ ተቀባዩ ሀገር፣ እንደሚላከው የሰው ኃይል ክህሎት ወይም የሙያ ዓይነት መሰረት ሊለያይ ይችላል።

ንዑስ ክፍል ሁለት

ለሠራተኞች ስለሚደረግ ድጋፍ

፸፩. ኃላፊነት

፩/ ሚኒስቴሩ እና እንደ አግባቡ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በውጭ ሀገር ለሥራ የተሰማራ ሠራተኛ መብት፣ ደህንነትና ክብር መጠበቁን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፪/ ማንኛውም ኤጀንሲ ለሥራ የላከውን ሠራተኛ አስመልክቶ አሠሪው በሥራ ውሉ መሠረት ያለበትን ግዴታዎች እንዲያከብር የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

፫/ የማሰልጠኛ ተቋማት እና የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ተቋማት የተጣለባቸውን ሃላፊነት የመወጣት ግዴታ አለባቸው።

፸፪. ስለድጋፍ አሰጣጥ

፩/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን ከውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ጋር በተያያዘ ከሠራተኛው ወይም ስለሠራተኛው ያገባኛል ከሚል ሰው የሚቀርብ የድጋፍ ጥያቄ በመቀበል ሊያስተናግድ ይችላል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ስለቀረበው የድጋፍ ጥያቄ ወይም ሠራተኛው ስለገጠመው ችግር ኤጀንሲው ተገቢውን መፍትሄ በመስጠት ሠራተኛው ስላለበት ሁኔታ ሪፖርት እንዲያቀርብ ያዛል፡፡

6/ The commission received by Agencies may vary depending on the country of destination, the skill level and the kind of profession of the worker to be deployed.

SUB-SECTION TWO

PROVISION OF SUPPORT TO WORKERS

71. Responsibility

1/ The Ministry and, as appropriate, the Ministry of Foreign Affairs shall have the responsibility to ensure that the rights, safety and dignity of workers deployed in overseas employment are respected.

2/ With respect to a worker it has deployed, any agency shall have a duty to cause the employer respect obligations enshrined in the contract of employment.

3/ Training institutions and one stop service centers shall discharge responsibilities imposed on them.

72. Provision of Support

1/ The Ministry or the appropriate authority may entertain requests for support, presented by the worker or a person who has concern for the worker, in connection with issues of overseas employment.

2/ When support is requested pursuant to Sub-Article (1) of this Article, the Ministry or the appropriate authority shall order the Agency to take remedial actions regarding the support sought or problem encountered by the worker, and to submit report on the status or condition of the worker.

https://ethiodata.et/

፫/ በሠራተኛ ወይም ስለ ሠራተኛው ያገባኛል ከሚል ሰው ለሚቀርብ የድጋፍ ጥያቄ የሚመለከተው ኤጀንሲ ወይም አሠሪ ተገቢውን መፍትሂ ካልሰጠ ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ መሠረት አስፈላጊውን አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

፬/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው ባለስልጣን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ከውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት በኋላ የሚመለሱ ዜጎች የፋይናንስ፣ የስልጠና፣ የኢንተርፕርነርሺፕ፣ የመሳሰሉትን ድጋፎች አግኝተው በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ በመሳተፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል።

**፸፫. <u>በፈቃድ ወይም ለዕረፍት ወደ ሀገር የሚመጣ ሠራተኛን ስለመመዝገብ</u>**

፩/ በፈቃድ ወይም ለዕረፍት ወደ ሀገር የሚመጣና ይሰራበት ወደ ነበረው አሠሪ የሚመለስ ሠራተኛን በተመለከተ የሚከተሉት ሰነዶች በሥራ ገበያ መረጃ ስርዓት ተመዝግበው ለሚኒስቴሩ መቅረብ ይኖርባቸዋል፦

ሀ) የፀና ፓስፖርት፤

ለ) ወቅቱ ያላለፈበት ቪዛና የሥራ ፈቃድ በሚመለከተው አካል የተረጋገጠ፤

ሐ) ልዩ የሥራ ቁጥር መውሰድ (ከዚህ በፊት ያላወጣ ከሆነ)፤

መ) በሚኒስቴሩ የሚጠየቁ ሌሎች ማስረጃዎችን።

፪/ የሥራ ፈቃድ ግዜያቸው ያበቃ እና በድጋሚ የሚመለሱ ሠራተኞች በተመለከተ ቀድሞ ይሰሩበት የነበረውን አሠሪ ካልቀየሩ:-

3/ Where the Agency or the employer fails to take remedial action, in response to the support requested by the worker or a person who has concern for the worker, the Ministry or the appropriate authority may take the necessary administrative measure in accordance with this Proclamation.

4/ The Ministry or the appropriate authority shall, in cooperation with concerned bodies, facilitate financial, training, entrepreneurial and similar supports for overseas workers who returned home to enable them benefit by participating in economic activities; the details of its implementation shall be specified in a directive.

**73. <u>Registration of Returning Workers on Leave or Vacation</u>**

1/ The following documents of any worker coming to his homeland, being on leave or vacation, and returning back to same employer shall be registered in the labor market information system and presented to the Ministry:

a) valid passport;

b) valid visa and work permit confirmed by the concerned body;

c) obtain work identification number (if not already obtained);

d) other evidence requested by the Ministry.

2/ Regarding a worker whose work permit has expired but seeks to return to the same employer:

https://ethiodata.et/

ሀ) የፀና ፓስፖርት፤

ለ) ወቅቱ ያላለፈበት ቪዛና የሥራ ፈቃድ በሚመለከተው አካል የተረጋገጠ፤

፫/ የሥራ ውላቸው ያበቃ እና ወደ ሀገር ሳይመለሱ በነበሩበት አሠሪ የሥራ ውላቸውን ማደስ ወይም መቀጠል የሚፈልጉ ሠራተኞችን በተመለከተ

ሀ) የፀና ፓስፖርት፤

ለ) ያበቃውን የሥራ ውላቸውን ለመቀጠል ወይም ለማደስ የተስማሙበትን የውል ሰነድ፤

ሐ) ወቅቱ ያላለፈበት ቪዛና የሥራ ፈቃድ በሚመለከተው አካል የተረጋገጠ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

## ንዑስ ክፍል ሦስት
## ስለማስማማት እና ሠራተኛን ወደ ሀገር ስለመመለስ

**፸፬. ስለማስማማት**

ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው ባለሥልጣን ከውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ጋር በተያያዘ እንደ ጉዳዩ ተገቢነት በሠራተኛ፣ በኤጀንሲ ወይም በአሠሪ ላይ የሚቀርብ አቤቱታን ተቀብሎ ሊያስማማ ይችላል፡፡

**፸፭. ስለማስማማት ሂደት**

፩/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው ባለሥልጣን አቤቱታን በተቀበለ በሦስት የሥራ ቀናት ውስጥ አቤቱታ ለቀረበበት አካል በማሳወቅ ሁለቱ ወገኖች ቀርበው ጉዳዩን በ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ በስምምነት እንዲጨርሱ ጥረት ያደርጋል፡፡

a) valid passport;

b) valid visa and work permit confirmed by the concerned body.

3/ With respect to workers whose employment contracts have expired and who wish to renew or extend their employment contracts with their current employer without returning to Ethiopia, they shall be required to submit the following:

a) valid passport;

b) contractual document evidencing their agreement to renew or extend their expired employment contract;

c) valid visa and work permit attested by the relevant authority.

## SUB-SECTION THREE
## CONCILIATION AND REPATRIATION OF WORKERS

**74. Conciliation**

The Ministry or the appropriate authority may receive and conciliate any complaint submitted to it against a worker, an Agency or employer relating to overseas employment.

**75. Conciliation Proceedings**

1/ The Ministry or the appropriate authority shall, upon receipt of a complaint, notify the respondent within three working days and strive to bring both parties together and cause them to arrive at an amicable settlement within fifteen working days.

https://ethiodata.et/

፪/ ስምምነት የተደረሰባቸው ጉዳዮች በጽሁፍ ሆነው በሁለቱ ወገኖች ላይ አስገዳጅነትና ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

፫/ የማስማማቱ ጥረት ካልተሳካ አቤቱታ አቅራቢው ጉዳዩን ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለሥልጣን በአምስት የሥራ ቀናት የአቤቱታ መወሰኛ ሥራ ክፍል ማቅረብ ይችላል፡፡

## ፸፮. ሠራተኛን ወደ ሀገር የመመለስ ግዴታ

፩/ ማንኛውም ኤጀንሲ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል ፦

ሀ) የሥራ ውል እንደተቋረጠ የአየር ትራንስፖርት ወጪን በመሸፈን ሠራተኛውንና የግል መጠቀሚያ ንብረቶቹን ወደ ሀገሩ የመመለስ፤

ለ) ሠራተኛው ከባድ የአካል ጉዳት ሲደርስበት ወይም ሲሞት ጉዳት የደረሰበትን ሠራተኛ ወይም አስከሬን የሚቆይበት በቂ ምክንያት ከሌለ በስተቀር ከግል መጠቀሚያ ንብረቶቹ ጋር የአየር ትራንስፖርት ወጪ በመሸፈን ሠራተኛው ስለደረሰበት ጉዳት ወይም ሞት ከሚገልጽ ሕጋዊ የህክምና ማስረጃ ጋር በማያያዝ በ፲፭ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ወደ ሃገሩ የመመለስ እና ተያያዥነት ያላቸው ሌሎች ወጪዎችን የመሸፈን፤

ሐ) የሥራ ላይ ጉዳት የደረሰበት ሠራተኛ ወደሀገር ሲመለስ አስፈላጊ ገንዘብ ወጪ በማድረግ ሕክምና እንዲያገኝ የማድረግ፡፡

2/ The issues on which amicable settlement is reached shall be binding and enforceable.

3/ Where efforts for amicable settlement fail, the complainant may submit his case to the adjudication office of the Ministry or of the appropriate authority within five working days.

## 76. Repatriation of Workers

1/ Any Agency shall have the following obligations:

a) transporting back the worker and his personal belongings by covering air transport fee upon termination of contract of employment;

b) where the worker sustains serious bodily injury or dies, unless there is valid reason for delay, repatriating the injured worker or his body and personal effects accompanied with legal medical certificate witnessing his injury or death within 15 consecutive days and shall cover all expenses of air transport associated with the repatriation;

c) covering medical expenses to a worker who has been repatriated due to serious bodily injury.

https://ethiodata.et/

፪/ ሠራተኛው የሥራ ውሉን ያለበቂ ምክንያት ካቋረጠ ኤጀንሲው ሠራተኛውን ወደአገሩ በመመለስ ያወጣውን ወጪ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

2/ Where the worker terminates his contract of employment without good cause, the Agency may claim reimbursement for expenses incurred in repatriating the worker.

**፸፯. በውጭ ሀገር ለተሰማሩ ሠራተኞች ድንገተኛ አደጋ ምላሽ ስርዓት**

በውጭ ሀገር ለሥራ የተሰማሩ ዜጎች ድንገተኛ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋ፣ ወረርሺን እና መሰል ሁኔታዎች ተከትሎ ዜጎች በብዛት ወደ ሀገር መመለስ ሲያስፈልግ ሥራ ላይ የሚውል ሥርዓት ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና አግባብነት ካለች የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና ተቋማት ጋር እንዲዘረጋ ያደርጋል፣

**77. Emergency Response Mechanism for Overseas Workers**

In collaboration with the Ministry of foreign affairs and other concerned ministries and institutions, there shall be established a system for handling urgent natural or manmade disaster, epidemic and similar emergencies that necessitate mass repatriation of citizens deployed in overseas employment.

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## PART SEVEN

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**፸፰. ስለ ግንዛቤ ማሳደጊያ ፕሮግራም**

ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን ፡-

፩/ ለሥራ ወደ ውጭ ሀገር ለመሄድ ፍላጎት ላላቸው ዜጎች ስለተቀባይ ሀገር ሁኔታ፣ በሚሰማሩበት የሥራ መስክ ሊኖራቸው ስለሚገባ ክህሎት፣ ስለመብታቸውና ኃላፊነታቸው እና ስለመሳሰሉት ጉዳዮች የቅድመ-ስምሪትና የቅድመ-ጉዞ ግንዛቤ ማሳደጊያ ሥልጠና በመደበኛነት ይሰጣል፤

፪/ ከኤጀንሲ ፌደሬሽን ጋር በጋራ የግንዛቤ ማሳደጊያ መድረኮችን በማዘጋጀት ለማህበረሰቡ ግንዛቤ እንዲፈጠር ያደረጋል፤

**78. Awareness Creation Program**

The Ministry or the appropriate authority shall:

1/ Provide pre-deployment and pre-travel awareness creation training to workers desiring to engage in overseas employment regarding the situation in the destination country, the skill they need to have in the destination country, their rights, responsibilities and similar matters;

2/ Create, together with Agency federation and federation board members, awareness to the general public by organizing awareness creation program;

https://ethiodata.et/

፫/ ሕብረተሰቡ ስለውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ተጨባጭ ሁኔታ ትክክለኛ እና ወቅታዊ መረጃ እንዲያገኝ የመገናኛ ብዙኃንን በመጠቀም ቀጣይነት ያለው ሃገር አቀፍ የግንዛቤ ማሳደጊያ ሥራዎችን ያከናውናል፤

፬/ ለኤጀንሲ የቦርድ አመራሮች፣ ሥራ አሥኪያጆች እና ሠራተኞች ስለውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማሳደጊያ ፕሮግራሞችን ያካሂዳል፤

፭/ ስለ ኢትዮጵያዊያን ሠራተኞች ምልመላና ቅጥር ሁኔታ፣ ስለውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት በሥራ ላይ ስላሉ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ቅድመ ሁኔታዎች እና የተለያዩ መስፈርቶች ለውጭ ሀገር አሠሪዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ገለፃ ይሰጣል፡፡

**፸፱. ስለኤጀንሲና ወኪል ጥምረት**

በተቀባይ ሀገር ሥራና ሠራተኛ ለማገናኘት የሚያስችል ፈቃድ ያለው ወኪል በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ከምን ያህል ኤጀንሲዎች ጋር ወኪል ሆኖ መሥራት እንደሚችል እንዲሁም ፈቃድ ያለው ኤጀንሲ በተቀባይ ሀገር ፈቃድ ካለው ምን ያህል ወኪል ጋር መሥራት እንደሚችል ሚኒስቴሩ በመመሪያ ይወስናል፡፡

**፹. ስለ ሥራ ክርክር አፈታት**

በሠራተኛ እና በአሠሪ ወይም በኤጀንሲ መካከል ካለው የሥራ ግንኙነት በመነጨ የሚነሳ ማናቸውም የመብትና የጥቅም ክርክር ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ መሠረት በተቋቋመ የሥራ ክርክር ችሎት ይታያል።

3/ Undertake awareness creation activities using mass media in order to provide the general public with actual and up-to-date information regarding overseas employment;

4/ Undertake regular awareness creation program for board members, general managers, and employees of Agencies;

5/ Inform foreign employers regarding recruitment and employment of Ethiopian workers, laws, Regulations, Directives, preconditions, and other standards applicable to overseas employment.

**79. Matrix of Agencies and Representatives**

The Ministry shall determine by directive the number of Ethiopian Agencies that a single licensed representative in the country of destination may represent, and the permissible number of representatives in the country of destination with whom an Ethiopian Agency may work.

**80. Labor Dispute Resolution**

Any dispute arising between the worker and the employer or an Agency in connection with rights and interests shall be resolved before a Labor Bench established pursuant to Labor Proclamation.

https://ethiodata.et/

**፹፩. የማስረዳት ግዴታ**

በዚህ አዋጅ መሠረት ለሥራ ወደ ውጭ ሀገር የሚሄድ ሠራተኛ በሥራ ሁኔታዎች ላይ የሚያቀርበውን ክስ ወይም አቤቱታ ኤጀንሲው ወይም አሠሪው ከተቃወመ ክሱ ወይም አቤቱታው ሊደገፍ እንደማይገባ የማስረዳት ግዴታ የሚወድቀው በኤጀንሲው ወይም በአሠሪው ላይ ይሆናል።

**፹፪. ስለ ይርጋ**

በዚህ አዋጅ መሠረት በአሠሪ፣ በኤጀንሲ፣ በኤጀንሲ ወኪል ወይም በሠራተኛ በሚፈፀም ጥፋት ምክንያት የሚቀርብ ማንኛውም አስተዳደራዊ አቤቱታ ጥፋቱ ከተፈፀመበት ወይም ጥፋቱ መፈፀሙ ከታወቀበት ቀን አንስቶ እስከ ሶስት ዓመት ድረስ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው ባለሥልጣን ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡

**፹፫. ክልከላ**

፩/ ማንኛውም ሰው ሠራተኛን ገንዘብ በማስከፈል የውጭ ሀገር ሥራና ሠራተኛ የማገናኘት ተግባር ማከናወን የተከለከለ ነው፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ለሥራ ወደ ውጭ ሀገር የሚሄዱ ዜጎች የሚሄዱበት ሀገር በጦርነት ቀጠና፣ በተፈጥሮ አደጋ ወይም በበሽታና በመሳሰሉት ምክንያቶች ለዜጎች ደህንነት አስጊ መሆኑን ካመነ ለሥራ ተቀጥረው እንዳይሄዱ ሊከለክል ይችላል፡፡

፫/ ከአንድ ማዕከል አገልግሎት ጀምሮ በተዘረጋው የኢትዮጵያ የሥራ ገበያ ሥርዓት ውጪ የሚደረግ ማናቸውም የሠራተኛ ምልመላና ስምሪት ተግባር የተከለከለ ነው።

**81. Burden of Proof**

Whenever a worker deployed for overseas employment institutes a court case pertaining to work conditions and if the employer or the Agency objects to the suit or complaint, the burden of proof lies on the Agency or the employer to show that the action does not have a legally valid ground.

**82. Period of Limitation**

Any administrative complaint against an employer, Agency, representative of Agency or a worker regarding commission offences pursuant to this Proclamation shall be barred by limitation unless submitted to the Ministry within three years from the date of commission of the offence or from the time the commission of the offence was known.

**83. Prohibition**

1/ It is prohibited for any person to undertake overseas employment service by taking payments from a worker.

2/ The Ministry may prohibit the departure of citizens for overseas employment whenever the country of destination is believed to be a war-zone, affected by natural calamities or contagious diseases and for similar reasons which endanger the safety of citizens.

3/ Any recruitment and deployment of workers conducted outside of the established labor market information system, which commences at one stop centers, is prohibited.

https://ethiodata.et/

**፹፬. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚያስፈልገውን ደንብ ያወጣል ፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ለዚህ አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወጣውን ደንብ ለማስፈፀም መመሪያ ያወጣል ፡፡

**፹፭. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፹፮. የተሻሩ ሕጎች**

፩/ ስለ ሥራና ሠራተኛ ማገናኘት አገልግሎት የወጣ አዋጅ ቁጥር ፱፻፳፫/፪ሺ፰ እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፵፮/፪ሺ፲፫ ተሽሯል፡፡

፪/ ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

**፹፯. ተፈጻሚነት ስለሚኖራቸው ሕጎች**

በአዋጅ ቁጥር ፱፻፳፫/፪ሺ፰ እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፵፮/፪ሺ፲፫ መሠረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች እስከሚተኩ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል፡፡

**84. Power to Issue Regulation and Directives**

1/ The Council of Ministers shall issue Regulations for the proper implementation of this Proclamation.

2/ The Ministry shall issue Directive for the proper implementation of this Proclamation and the Regulation to be issued pursuant to Sub-Article (1) of this Article.

**85. Duty to Cooperate**

Any person shall have duty to cooperate for the proper implementation of this Proclamation.

**86. Repeal and Inapplicable Laws**

1/ Overseas Employment Proclamation No. 923/2016 and its amendment Proclamation No. 1246/2021 are hereby repealed.

2/ No law, Regulations, Directives or practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, be applicable in respect of matters provided for in this Proclamation.

**87. Applicable Laws**

Regulations and directives issued pursuant to Proclamation No. 923/2016 and its amendment Proclamation No. 1246/2021 shall, in so far as they are not inconsistent with this Proclamation, remain in force until replaced by regulations and Directives to be issued pursuant to this Proclamation.

https://ethiodata.et/

**፹፰. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፮ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም:-

፩/ ለሥራ ወደ ውጭ ሀገር የተላከን ሠራተኛ በሚመለከት ይህ አዋጅ ከመፅናቱ በፊት በማናቸውም የሥራ ክርክር ሰሚ አካል ዘንድ በመታየት ላይ ያለ የሥራ ክርክር በተጀመረበት ሕግና ሥርዓት መሠረት ፍፃሜ ያገኛል፡፡

፪/ በአዋጅ ቁጥር ፱፻፳፫/፪ሺ፰ መሠረት ሠራተኛን በውጭ አገር ለሥራ ለማሰማራት ፈቃድ ተሰጥቶት የነበረ ማንኛውም ኤጀንሲ ሥራውን መቀጠል የሚፈልግ ከሆነ ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን ጀምሮ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ አዲስ ፈቃድ ማውጣት አለበት፤ በዚህ ጊዜ ውስጥ አዲስ ፈቃድ ሳያወጣ ቢቀር ቀድሞ ተሰጥቶት የነበረው ፈቃድ ዋጋ አልባ ይሆናል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የተደነገገው ቢኖርም ፈቃዱ የተሰረዘበት ኤጀንሲ ለሥራ ወደ ውጭ ሀገር የላካቸው ሠራተኞች ከሚያነሱት ማናቸውም የመብት ጥያቄ ነፃ አያደርገውም፡፡

**88. Transitory Provisions**

Notwithstanding the provisions of Articles 86 Sub Article (1);

1/ Any dispute pertaining to overseas employment pending before any competent organ to settle labor disputes prior to coming into force of this Proclamation shall be settled in accordance with the law and procedure which were in force before coming into force of this Proclamation;

2/ Any agency previously licensed to engage in overseas employment of workers under Proclamation No. 923/2016 that wishes to continue its operations shall obtain a new license within three months from the effective date of this Proclamation; failure to acquire a new license within this period shall render its former license null and void.

3/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (2) of this Article, the revocation of an agency’s license shall not absolve it from any claim of right raised by workers it deployed overseas.

https://ethiodata.et/

**፹፱. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሀሴ ፰ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም**

**ታዬ አጽቀ ሥላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት**

**89. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 14th day of August ,2025.**

**TAYE ATSKESELLASSIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

https://ethiodata.et/